# ሰብዓቱ አጽርሓ መስቀል

Updated version





www.ethiopianortodox.org

**ማውጫ** — ገጽ

፩. የመጀመሪያዉ ቃል « አባት ሆይ የሚሠሩትን አያዉቁምና ይቅር በላቸዉ» 7
፪. ሁለተኛዉ ቃል «እዉነት እልሃለሁ ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ» 15
፫. ሦስተኛዉ ቃል «አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ . . እናትህ እነኋት 25
፬. አራተኛዉ ቃል «አምላኬ አምላኬ ለምን ተዉኸኝ» 29
፭ አምስተኛው ቃል «ተጠማሁ» 34
፮ ስድስተኛ ቃል «ተፈጸመ» 36
፯ ሰባተኛው ቃል «አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ» 39
ማጠቃለያ 41
ግብረ ሕማማት
- ድርሳነ ዘአባ ሕርያቆስ 47
- ድርሳን ዘቅዱስ ዲዮናስዮስ 49
- ድርሳነ ዘአባ ያዕቆብ ዘሥሩግ 50

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ጠብቆ የወጣ ትምህርት፡፡

የጽሑፉ ምንጭ ፤ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ፡፡

" the seven words of our LORD on the cross"

ሕትመትና ሥርጭት፤ - ዬT



www.ethiopianortodox.org

# መግቢያ

ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ ለሁላችን ሕይወትን የዘሩ ሰባት ቃላትን ተናግሮ ነበር። ለፍርድ ባቀረቡት ም ጊዜ ሆነ በማንገላታት ሕማምን ሲያደርሱበት የተናገረባቸው ወቅቶች እጅግ ጥቂት ናቸው። የገዛ መብቱን አሳልፎ ሰጠ ክብሩንም ሲያዋርዱ በፈቃዱ ዝም አላቸው ። ፍቅር ገንዘብዋን አትሻምና ( የራሱን አይፈልግምና ) (፩ቆር፲፫፥፭)።

በመስቀል ላይ ሳለ ግን ተናገረ። መናገሩም ለእኛ ሲል ፤ ለእኛው ጥቅምና ድኅነት ነበር ። እያንዳንዱ ቃል የራሱ የሆነ ታላቅ ምሥጢር ስላለው በጥልቀት የምንመለከተው ይሆናል ። ለአሁን ግን ጌታ የተናገራቸውን ነገሮች በተመለከተ ጠቅለል ባለ መልኩ የሚከተሉትን ነጥቦች ለማስቀመጥ እንወዳለን ።

ጌታ በመስቀል ሳለ በተናገረው ቃላት ውስጥ ታላቅ ስጦታውን እናያለን። አምላካችን በሕመም ላይ ሆኖ እያለ እንኳ ሰጪ ለጋስ ነበር ። ለጠላቶቹ ምሕረትን ፣ በቀኙ ለተሰቀለው ወንበዴ መንግሥተ ሰማያትን ቡርክት ለሆነች እናቱ መንፈሳዊ ልጅን ጥበቃንና አይዞሽ ባይነትን ሰጥቷል። ለሚወደው ለዮሐንስም እመቤታችንን በቤቱ የማኖርን በረከት ሰጠ፤ ለእርሱ ግን ማንም ምንም የሰጠው ነገር የለም። ለሰው ወገን ይህን ሁሉ ሰጠ፤ የሰው ወገን ግን ለእርሱ በምላሹ ከመስቀልና ከሆምጣጤ በቀር አንዳች የሰጠው ነገር የለም።

ጌታ በመስቀል ከተናገራቸው ሰባት ቃላት የመጀመሪያውና የመጨረሻው ወደ አብ የተነገሩ (ለአብ የተናገራቸው) ናቸው። በመጀመሪያው ቃሉ «አባት ሆይ ይቅር በላቸው » ሲል ተናገረ ። (ሉቃ ፳፫፥፴፬)

በመጨረሻው ቃሉ ለአብ «በእጅህ ነፍሴን አደራ እሰጣለሁ» ሲል ተናገረ ። (ሉቃ ፳፫፥፵፮)

በመጀመሪያው እና በመጨረሻው ቃላቶች መካከልም ወደ አብ የተናገራቸው ሁለት ሌሎች ቃላት አሉ። በማቴ ፳፯፥፵፮ ላይ «አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ ?» የሚለውንና በዮሐንስ ፲፱፥፴ «ሁሉ ተፈፀመ » የሚለው ይህ የመጨረሻው ቃል ስለሆነው ነገር ሁሉ ጠቅለል ብሎ



www.ethiopianortodox.org

የተናገረው ቃል ቢመስልም ነገር ግን  የተናገረው ወደ አብ ነው፡፡ «አደርገው ዘንድ የሰጠኸኝን ሥራ ፈጸምሁ »(ዮሐ ፲፯:፬ ) ስለዚህ ጌታ በመስቀል ከተናገራቸው ቃላት አብላጫው አራት የሚሆኑት  ወደ አብ የተናገራቸው ናቸው በተጨማሪም ለሰው ልጅ የድኅነትና የሰላም ማረጋገጫ ዋስትና የሰጡ ቃላት ናቸው ፡፡

አብን ሲያናግር በሁለት አጠራር መሆኑንም ከንግግሩ እንረዳለን፡፡አባት ሆይ በሚልና አምላኬ በሚል፡፡አባት ሆይ በሚለው ቃሉ የእግዚአብሔር  ልጅስ እንደሆንህ ከመስቀል ውረድ ሲሉ የተፈታተኑትን የረታቸው  የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሰጠ፡፡ (ማቴ ፳፯:፵)

ነገር ግን መስቀሉ ወደ ሰማያት እንዲወጣ አደረገ እንጂ እርሱ ከመስቀል አልወረደም ፡፡ ማለት መከራን የተቀበለው ያ የተቸነከረው ሥጋ በአብ ዕሪና ተቀመጠ ፡፡

አምላኬ በሚለው ቃሉ  ደግሞ ሰው መሆኑን አፅንቶ አሳወቀ በሁለቱ ቃላት በአንድነት፤ ሰው ሆኖ የተገለጠው የተወለደው አምላክ እርሱ እንደሆነ ገልጦ ተናገረ ፡፡ እርሱም በሥጋ የተገለጠ  ነው (፩ጢሞ ፫:፲፮)  አባት ሆይ በሚለው ቃሉ የክርስቶስን አምላክነት የካደውን የአርዮስን ትምህርት ረታ ፤ አምላኬ በሚለው ቃሉ ደግሞ የክርስቶስን ሰውነቱን ሰው መሆኑን የካደውን የአውጣኪን የሐሰት ትምህርት ረታ ፡፡ አባት ሆይ ሲል የእግዚአብሔር ልጅ እንደመሆኑ መጠን ተናገረ አምላኬ ሲል የሰው ልጅ እንደመሆኑ መጠን ተናገረ፡፡

በመስቀል ሳለ የተናገረው ወደ አብ ብቻም አይደለም ፤ ወደ ሰው ልጆችም ጭምር እንጂ፡፡ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም እና በሐዋርያው በቅዱስ ዮሐንስ ምሳሌነት ቅዱሳንን፤ በቀኙ በተሰቀለው ወንበዴ ምሳሌነት ስለኃጢአታቸው ያዘኑ፣ የተፀፀቱ ኃጥአንን አነጋግሯል ፡፡

ቃላቱ የበረከትና የጸጋ፣ የመስቀሉ ጊዜም የድኅነት ጊዜ ነበር ያ ድኅነትም ደስታ ሁሉ ሊያደረግለት የሚገባው ነው፡፡ ስለዚም ጌታችን በመስቀል ላይ ሳለ የይቅርታን የድኅነትን እና የዘለዓለማዊ ሕይወትን ቃል ተናገረ እነዚህም የማያልቅ ስጦታና የጸጋ ቃል ናቸው ፡፡ በመስቀሉ ሳለ ምንም እንኳ ብዙ ሕማም የደረሰበት ቢሆንም በማንም



www.ethiopianortodox.org

ላይ አልፈረደም፤ አንድን ሰው እንኳ አልቀጣም ፡፡ ዓለምን ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣምና፡፡

ጌታ በመስቀል ሳለ የተናገራቸው ቃላት የመንፈስ አቅጣጫቸው አንድ ትርጉም እንዲሠጥ ነው፡፡ በእርሱም ያለው ጥበብ የማያሳስት ግልጽ ነው፤ ቅድሚያ ለሌሎች ፤ ከዚያ በኋላ ለእኔ የሚል ፡፡ እርሱነቱ ስለሌሎች ጥቅም ነበር ፡፡ በመስቀል ሳለ ቅዱስ ደሙ የድኅነት መሣሪያነቱን ውጤት ማስገኘት ጀምሮ ነበርና ጌታም ለሰው ልጆች ይቅርታን፣ ምሕረትን በመጠየቅ መናገረ ጀመረ ፡፡ ድኅነት ተቃርቦ ሳለ ደግሞ የገነትን ዳግም መከፈት የሚያበሥረው ሁለተኛው የጌታ ቃል መጣ ፡፡ የመዳን ዋጋዋ በደም እስከተከፈለ ድረስ ገነት መከፈቷ የማይቀር ነበርና ፡፡

ጌታ ወዳጆቹን አንሥቶ ከመናገር በፊት ጠላት ሆነው የነበሩትን አስቀድሞ እንደነበርም እናያለን ፡፡ የመጀመሪያው እና ሁለተኛው ቃሉ የሚያንገላቱትንና በደለኞቹን የሚመለከት ነበር ፡፡ ከዚያ ለእመቤታችንና ለቅዱስ ዮሐንስ ፡፡

ወደ እግዚአብሔር አብም ሲናገር አስቀድሞ አባቴ ብሎ ቀጥሎም አምላኬ ብሎ ነው ፡፡ አስቀድሞ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እንደመሆኑ ተናገረ (ዮሐንስ ፩:፲፰) ቀጥሎ ደግሞ ዘመኑ በደረሰ ጊዜ የተወለደ የሰው ልጅ እንደመሆኑ መጠን ተናገረ፡፡

በመስቀል ሳለ ከተናገራቸው ቃላት የመጀመሪያው ሦስቱ የይቅርታ እና የቸርነት፤ የመጨረሻዎች አራቱ ደግሞ የማዳን ሥራ መፈጸሙን የሚያውጁ ነበሩ፡፡

«አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ» የሚለው ቃሉ አብ ወልድን የድኅነትን ዋጋ ይከፍል ዘንድ እንደተወው (አሳልፎ እንደሰጠው ያስረዳል፡፡)

በዮሐንስ ፲፱:፳፰ ላይ ተጽፎ የምናገኘው «ተጠማሁ» የሚለው ቃሉ ለሰው ልጅ ሲል ጌታ በሰውነቱ ( በአካሉ) ምን ያህል መከራን እንደተቀበለ ይጠቁማል፡፡ አሁን የጠቀስናቸው ሁለቱም ቃላት የእኛን ከኃጢአት ነፃ መሆኛ ዋጋ እየተከፈለ እንደነበር የሚያስረዱ ናቸው «ተፈጸመ» የሚለው ቃሉም ያ ዋጋ ተከፍሏል የሚል ትርጉም ያለው ነው፡፡«ነፍሴን



www.ethiopianortodox.org

በእጅህ አደራ እሰጣለሁ» የሚለው ቃል ደግሞ የኃጢያት ደመወዝ ሞት እንደሆነ ያሳያል ። በሞት አማካይነት ድኅነት ተገኘ። ስለዚህ በዚህ መልኩ የመጨረሻዎቹ አራት ቃላት ድኅነትን በተመለከተ ሆነ ( ተከናወነ) ብለው መተማመኛን ለሰው ልጅ የሚሰጡ ናቸው ።

በመጨረሻዎቹ ሁለት ቃላት ውስጥ የደስታና የድል ስሜትም አለ። እግዚአብሔር በእኒህ ቃላቱ ድኅነት እንዲገኝበት ምክንያት የሆነውን ሕማሙን እንደ ገለጠ፤ የድኅነት ሥራ በመጠናቀቁ የተሰማውን ደስታም እንዲሁ በዚሁ ገልጦበታል ።

በዮሐንስ (፲፱፡፴) ላይ የምናገኘው «ተፈጸመ» የሚለው ቃል ድኅነት በተሟላ መልኩ እንዲከናወን የሚያስፈልጉት ነገሮች በሙሉ መሟላታቸውን ያሳያል ። እግዚአብሔር አቅዶት የነበረው ተግባር በመከናወኑ ደስ ተሰኘ ፤ ያንን ዓላማ የሚያደናቅፍ ነገር እንዲከሠትም አልፈቀደም ። «ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ » የሚለው ቃሉ ትርጓሜም እንዲሁ ነው ። በሁለቱ የመጨረሻ ቃላቱ አማካይነት የሰይጣንን ድል መሆን አወጀ። በሞት እግዚአብሔር የሞትን ኃይል አስቀረው ፤ ከዚያም የደስታ፣ የድል አድራጊነት ድምፅ ተሰማ።

እስከአሁን የገለጥናቸው ቃላት ጌታ በመስቀል ተሰቅሎ ሳለም እንኳ ለእኛ እየሠራ እንደ ነበረ በሚገባ ያስተምሩናል ።ለእኛ ድኅነትን እያስገኘልን የነበረ ብቻ አይደለም ፤ የመምህርነት እና የቸር ጠባቂነት ሥራውንም ቀጥሎ ነበር እንጂ ።

ድኅነትን በተመለከተ ዐቢይ የሆኑ አዲስ እውቀቶችንም (ግንዛቤዎችንም) እየገለጠልንም ነበር።

በመጀመሪያው ቃሉ ጠላቶቻችንን እንዴት መታገስ ፣ይቅር ማለት እና መውደድ እንደምንችል በተግባር አሳየን። « ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ» በሚለው የመጨረሻ ቃሉ ነፍስ የማትሞት እንደሆነች ፣ ጻድቅ ነፍስ ከሞት በኋላ ወደ እግዚአብሔር ከፍ ከፍ እንደምትል ገለጸልን።

በሦስተኛው ቃሉ ስለ እውነተኛ ፍቅርና አሳቢነት አስተማረን። እናቱንም በማክበር ከአሥርቱ ትዕዛዛት አምስተኛውን እንዴት በእውነትና በተግባር ልንፈጽመው እንደምንችል አስተማረን ።



www.ethiopianortodox.org

ከሰባቱ ቃላት የምንማረው ቁምነገሮችና የምንወስዳቸው ቅልልቅ ግንዛቤዎች ምንኛ ብዙ ናቸው ! ከቁጥር ወገንስ ሰባት ቁጥር ምንኛ ፍጹም ነው ! እስቲ ጌታ በመስቀል የተናገራቸውን ሰባቱን ቃላት ትርጓሜያቸውን በሚገባ ለመረዳት እያንዳንዱን ቃል በየተራ እንመልከተው፡፡

## *የመጀመሪያ ቃል*

### «አባት ሆይ ፤ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው»
### (ሉቃስ ፳፫:፴፬ )

ቸር አምላካችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ይግባውና በመስቀል ሆኖ ጥልቅ ሕማምን በመቀበል ላይ ሳለ ስለራሱ እያሰበ አልነበረም ፤ የሌሎች ነገር ያስጨንቀው ነበር እንጂ፡፡ ስለራሱ ሕማም ፣ ስለድካሙና ስለመቁሰሉ ሲያስብ አልነበረም፡፡ በጀርባው ላይ ያረፈው አለንጋ የፈጠረው ጥልቅ ቁስል አላሳሰበውም እጆቹንና እግሮቹን በስተው የያ ዙት አምስቱ ቅንዋት ( ችንካሮች ሳዶር አላዶር ዳናት አዴራ ሮዳስ) አላሳሰቡትም፡፡ ብቸኛው ሐሳቡና ትኩረቱ ለሰው ልጆች ያለው ፍቅር ብቻ ስለነበረ ሌላውን ሁሉ ነገር ትኩረት አልሰጠውም፡፡ በመጀመርያ የታሰበው ነገር ጠላቶቹንና እያሰቃዩት ያሉትን ሰዎች ማዳን ነበር፡፡ በመስቀል ሳለ ከተናገራቸው ቃላት ሁሉ የመጀመርያው «አባት ሆይ ፤ የሚያደርጉትን አያቁምና ይቅር በላቸው» የሚለው ነበር (ሉቃ ፳፫:፴፬)

ጌታ ለወዳጆቹና ለራሱ ከማሰቡም በፊት አስቀድሞ ለጠላቶቹ አሰበ፡፡ ምሕረትንም በመጀመሪያ ለጠላቶቹ ሰጠ፤ ቀጥሎም መጀመሪያ በንቀት ለሰደበውና ኋላ ግን ላመነው በደለኛ ለነበረ ይቅርታን አደረገ ፡፡ ከዚያ እናቱን ደግሞ አሰባት፡፡ ከዚህ ሁሉ በኋላ ነው ስለ ራሱ መናገር የጀመረው ፡፡

አባት ሆይ ይቅር በላቸው የምትለዋን ቃል የተናገረው በሥጋው እጅግ ከፍተኛ የሆነውን ሕመም እየተቀበለ በነበረበት ሰዓት ነው፡፡ በዚያች ሰዓት ምሕረትን እየለመነላቸው ካሉት ሰዎች እጅግ ከባድ የሆነውን ስቃይና መከራ እየተቀበለ ነበር፡፡ ነገር ግን ሰዎች ለእርሱ ከነበራቸው ሊገለጽ የማይቻል ጭካኔና ክፋት ይልቅ እርሱ ምሕረትን



www.ethiopianortodox.org

እየለመነላቸው ነበር ፡፡ ከዚህ ሰው ደም ነፃ ነን ብለው ጥፋት የለብንም ለማለት አንድም ፍላጎት ያልነበራቸው ሰዎች ! ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን ብለው ጮኸው ለተናገሩ ሰዎች ! (ማቴ ፳፯፡፳፭) በበደል በእጃቸው የተገረፈውና ሕማምን የተቀበለው እርሱ ጎዳኄ በቀል መምህረ ንስሐ ሆነ ፡፡ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ፡፡ ብሎ ለጥፋታቸው ምክንያትን አቀረበላቸው ፍጹም በሆነ ፍቅሩ ጌታ እንዴት ድንቅ ነው ! ሊኮንናቸው አልቸኮለም ፣ በቀልንም አልፈለገም ፤ እንዳሻቸው ይሁን ብሎ ቸል በማለት ሊተዋቸውም አልወደደም ፡፡

ለእነርሱ በነበረው ፍቅር የሚያስባቸው ቀና በሆነ መልኩ ነበር ፤ ምሕረትን ያገኙ ዘንድ ወደደ ፡፡ ጥፋት የለባቸውም አለ ፤ በአብ ፊት ለበደላቸው ምክንያትን አቅርቦ ኃጢአታቸው ካለማወቅ የተነሣ እንጂ በሌላ አይደለም በማለት ጠበቃ ሆናቸው ፡፡

እኛ ግን ሰው እንደመሆናቸው የሠሩትን ሥራ ስናስብ ተደራራቢ የጭካኔን ወንጀል የፈጸሙ በደለኞች አድርገን እንቆጥራቸዋለን ፡፡ በካህናት አለቆች መካከል የእርሱ ዝና ክብር ለእኔ ይሁን ባይነት ፣ ቅንዓት፣ ጠላትነት፣ ስም ማጥፋት እና ተንኮል ነበረ ፡፡ በክፋት ከተነሣሱት ከሕዝቡ ወገን ደግሞ ያለአንዳች ማሰላሰልና ለማሰላሰልም ባለመፈለግ በጭፍን የተደረገ ይወገድ! አንፈልገውም! አንቀበለውም ባይነት ነበር፡፡ወታደሮችና የካህናት አገልጋዮችም ጭካኔን፣ ስድብን፣ማዋረድን፣ማንገላታትን ፣ ፈጽመዋል ጲላጦስም ቄሣርን ፈርቶ ሕሊናው ከሚነግረው ሌላ የሆነውን ነገር በማድረግ ፍትሕን አንድሏል፤የለሁበትም በማለት ቸልተኝነትን ወይም ግድየለሽነትን አንፀባርቋል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የተሠራው ወንጀል የግድያ፣ ማሰቃየት እና የሐሰት ምስክርን የማቆማቸው ጥፋት ነው ፡፡ ነገር ግን እንዲህ እንዲፈረድበት የሆነው እርሱ በቸርነቱ ይህን ሁሉ ሥራ ካለማወቅ የተነሣ እንደተደረገ ቆጠረው ፡፡

የሚደርጉትን አያውቁምና ብሎ ተናገረ ! በእርግጥም በመስቀል የተሰቀለው ጌታ ያለው ፍቅርን ቸርነቱ እንደምን ዕጹብ ነው! የቸርነቱ ስፋት ሄደው ሊደርሱበት አስበውም ሊረዱት የማይቻል ነው ፡፡

ጌታ ለጠላቶቹ ምሕረትን በማድረግ ብቻ ሳይሆን በዚህ ምድር ሳለ ያስተማረውን ትምህርት እየአንዳንዱን በተግባር ማሳየቱ ግልጽ ነው ፡፡



www.ethiopianortodox.org

አስቀድሞ በማቴ ፭:፵፬ ላይ እንዲህ ብሎ ነበር ። «ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፣ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ» ስለዚህም ጌታ በመስቀል ሳለ በተናገረው በመጀመሪያ ቃሉ የፈጸመው ይህን ለሰው ልጅ የሰጠውን ትዕዛዝ ነው ። ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚለውን ትምግርቱን በተግባር ፈጸመው ያንንም ሲፈጽም ድንቅ በሆነ ፍጹምነትና ታማኝነት ነው ።

የተወደድህ ወንድሜ «**አባት ሆይ ይቅር በላቸው** » ስለሚለው ቃል ምን ታስባለህ? እንዴት ታየዋለህ? በስቅለት ዕለትም ይሁን በሌላ በማናቸውም ቀን ይህ ን ቃል አስበህ ጌታ ሆይ ለጠሉኝ ፣ ላሰቃዩኝና ላንገላቱኝ ላሳደዱኝም ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር ትላቸው ዘንድ እለምናለሁ ብለህ የምትጸልይ ብትሆን ከክርስቶስ የቸርነትና የፍቅር ሥራ አንተም ተሳታፊ ትሆናለሁ።

አንተ አሁንም ጠላቶችህን የምትጠላቸውና ይቅር ያላልካቸው ከሆነ ክርስቶስ ለጠላቶቹ ምሕረትን ማድረጉ ለአንተ ምን ይረባሃል ? ምን ጥቅም ታገኛለህ? አሁንም በዚህ ምግባር ያለህ ከሆንክ ከጌታ ሥራ አልተሳተፍህምና ፣ መንገዱንም አትከተል ምና ፣በቸርነት ሥራው እርሱን ፈጽሞ አልመሰልኸውም፤ ተሳታፊም አይደለህም።

እንግዲያውስ ለእኛ እንደተደረገልን እንዲሁ እኛም ለሌሎች አድርገን ፤ሌሎችን ይቅር በማለት በይቅርታ የሚገኘውን ደስታና ጣዕም እናውቅ ዘንድ ክርስቶስ እኛን ይቅር በማለት በይቅርታ የሚገኘውን ደስታና ጣዕም እናውቅ ዘንድ ክርስቶስ እኛን ይቅር እንዳለን እወቅ።

የሰዎችን በደል ባሰብን ቁጥር ከልብ በሆነ ስሜትና ታማኝነት የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ልንል ይገባል ። ነገር ግን እንዲህ በምንል ጊዜ ጌታ ይህን ቃል ከተናገረበት ሁኔታ የእኛ የተለየ ነው ። ጌታ የሚለው ይህንን ነው ።

አባት ሆይ ፤ የኃጢአታቸውን ዋጋ ከፍያለሁና ፣ ዕዳም የለባቸውምና ይቅር በላቸው ፤ ሰማያዊ ፍርድ የጠየቀውን የፍትሕ ዋጋ አሟልቻለሁ፤ ዕዳቸውንም ሁሉ ከፍያለሁ፤ አሁን ይቅር በላቸው። እነሆ ስላሰቃዩኝ ሰዎችና ስለማይወዱኝም ሰዎች ፈንታ ሞትን ቀመስሁ ይቅር በላቸው ያልሁት እነኚህን ብቻም አይደለም በደሜ አማካይነት ዕረፍት የሚሹትን ሁሉ እንጂ ከአዳም ጊዜ አንሥቶ እስከዘለዓለም፤



www.ethiopianortodox.org

ከኃጢአታቸው ተጸጽተው የሚመለሱ ኃጥአንንም ሁሉ እንጂ። ወደዚህች ሰዓት የመጣሁት ስለዚህ ነውና አባት ሆይ ይቅር በላቸው (1ኛ ዮሐ ፲፪:፳፯)

የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ከተባለላቸው አንድ የጌታን ጎን በጦር የወጋው ወታደሩ ለንጊኖስ ነው። ቤተክርስቲያን ይህን ወታደር በዓመት ሁለት ጊዜ ትዘክረዋለች ሳያውቅ (የሠራውን ክፋት ሳይረዳ) ጌታን በጦር ወጋው ። ስለዚህ ጌታ ይቅር አለው ፤ ቀየረውም ። ለንጊኖስ በዘመኑ ያመነውንም መሰክረ ሰበከ። በጢባርዮስ ዘመነ በተደረጉ ብዙ ተአምራት አማካይነትም ጌታ የዚህን ሰው ቅድስና ገለጠ።

**«የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው»** ። የሚለውን ቃል እንዲገለጽባቸው ከሆኑት ወገን አንድ ሌላም ጻድቅ አለ። ክርስቲያኖችን እንደአውሬ ያሳድድ የነበረ ኃያል፣ ያሰቃያቸውና ይገድላቸውም በነበረው በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን ቀኝ እጅ የነበረና እንደ እገሌ ተብሎ ተነጻጻሪ የማይገኝለት ክፉና ጨካኝ -ሰው ነበር።

የሮማ ሹማምንት በሚገባ ሊያሰቃዩት ያልቻሉት ክርስቲያን የሚላከው ወደ እርሱ ነበር። በእርሱም እጅ ተሰምቶ በማይታወቅ አዲስና ምሕረት አልባ የጭካኔ ስልት እንዲሰቃይ ይደረጋል ።

ይህ ሰው ቅዱስ አርያነስ ይባላል። በወቅቱ አንጼና ተብላ የምትጠራ ከተማ አስተዳዳሪ ነበር (አሁን የግብፅ አንዲቷ ከተማ ስትሆን መጠሪያዋ ግን ተቀይሯል)። ብዙ ሺህ ክርስቲያኖችንም እጅግ መሪር በሆነ ጭካኔ ለሞት አሳልፎ የሰጠ ነው። የሚያደርገውን ነገር ሳያውቅ (ሳይረዳ) በክርስቶስ እስካመነበት ጊዜ ድረስ ክርስቲያኖችን በማሳደድ ቀጠለ ። ካመነ በኋላ ግን በሮማው ንጉሥ በዲዮቅልጥያኖስ እጅ ሰማዕትነት ተቀበለ። ስሙ በስንክሳር ላይ ተጽፏል ቤተክርስቲያንም ከታላላቅ አባቶች ወገን ቆጥራ ታስበዋለች ።

ሳዉልም የሚያደርጉትን ከማያውቁት ወገን ነበረ። በእያንዳንዱ ቤት እየገባ ወንዶችንም ሴቶችንም እየጎተተ ወደ ወኅኒ አሳልፎ ይሰጥ ነበር ( ዮሐ ፰:፫) ቤተክርስቲያንም በእርሱ የተነሣ ትታወክ ነበር። ቀዳሚ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ እንዲገደል በማድረግም ተሳትፏል። (ሐዋ ፯:፶፰) ነገር ግን ሳዉል ወደ ደማስቆ ለመሄድ በመንገድ ሳለ ጌታ ራሱን ለሳዖል ገልጦ ምርጥ ዕቃ ሆኖ እንዲያጨው እስከሆነበት ጊዜ ድረስ



www.ethiopianortodox.org

የሚያደርገውን አያውቅም ነበር፡፡ ሳያል አምኖ በመጠመቁ የክርስቶስን ስም የሰበከ ያስተማረ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሆነ፡፡ ከሌሎች ሐዋርያት ሁሉ ይልቅ ተጋደለ ደከመም፡፡በብዙ ሕማምና እንግልትም በቄሳር ኔሮን እጅ ሰማዕትነትን ተቀበለ፡፡ ቤተክርስቲያንን በትምህርቱ ብርሃን ሆኖ ያገለገለ አንጸባራቂ ዓምድ አንዱ ሆነ፡፡ ጌታ በቸርነቱ አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ብሎ ባይናገር ኖሮ የቅዱስ ጳውሎስ አኳኋን (ፍጻሜ) ምን ይሆን ነበር?

አባት ሆይ ይቅር በላቸው ፤ ልበቀላቸው አልሻም(አልፈልግም) ክፋን በክፉ ለመመለስ አልፈልግም፡፡ አንዳንዶቹ መከራን ያደረጉብኝ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን አባት ሆይ ይቅር በላቸው ልበቀላቸው አልሻም ክፉን በክፉ ለመመለስ አልሻም፡፡አንዳንዶቹ መከራን ያደረጉብኝ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ሥፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ ፡፡ ወደእኔም እወስዳችኊለሁ ዮሐ ፲፬ ፥፫ ፡፡

**"አባት ሆይ ይቅር በላቸው"** ይህን ቃል ሲናገር ግን መከራ ያጸኑበትን ሁሉ አንድም ሰው ቢሆን ሁለት ዐበይት ነገሮችን አስቀድሞ ሳያሟላ ምሕረትን ሊያገኝ አይችልም፡፡ ሁሉቱ ነገሮች እምነትና ንስሐ ናቸው፡፡ ያለእምነት ና ንስሐ ማንም ሰው ድኅነትን እና ይቅርታን ሊያገኝ አይችልም፡፡ ስለዚህ የቃሉ ትርጓሜ አባት ሆይ የሚያምኑትንና በንስሐ የሚመላለሱትን ይቅር በላቸው የሚለውን ዐቢይ መልእክት የያዘ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና፡፡» መላውን ዓለም ወደደ ልጁንም ለመላው ዓለም ሰጠ ፡፡ ግን መላው ዓለም ድኅነትን አላገኛትም፡፡ ስለዚህ ነገርም ቀሪው የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እንዲህ ይላል ፤ « በእርሱ የሚያምን ሁሉ ዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ .... » (ዮሐ ፫፡፲፮ ) ይህ ለመዳን ማመን አንዱ ቅደመ ሁኔታ ለመሆኑ ጌታችን እንዲህ ይላል ነገር ግን « ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ » ( ሉቃ ፲፡፫፫) ስለዚህ ይቅር በላቸው የሚለው የምሕረት ጥያቄ በዘመናችን ላሉት የአይሁድ እምነት ተከታዮች የሚሠራ አይደለም አሁንም በአይሁድ እምነት ያሉት ጌታንም አናውቅም በማለታቸው፤ የቅድስት እናቱን ድንግልናም በመካድ ፀንተዋልና፡፡ ክብር ይግባውና አሁንም በናዝሬት የተወለደው ጌታ ሕዝቡን



www.ethiopianortodox.org

ሁሉ በትምህርቱ ያሳተ የሐሰት መምህር ነው ይላሉና፡፡ አያይዘውም አባቶቻቸው ጌታችንን ለሞት አሳልፈው መስጠታቸው ክብር ይግባውና የተገባ ነው ይላሉና፡፡ ስለዚህ ወገኖቻቸው በሠሩት ሥራ መስማማታቸው አባቶቻቸው በፈጸሙት ወንጀል ተባባሪ ያደርጋቸዋል፡፡ በዚህም ለፍርድ መቆም አይቀርላቸውም፡፡ ነገር ግን ንስሐ ቢገቡ አምነውም ክርስትናን ቢቀበሉ ፤ ጌታ ይቅር ይላቸዋል ከዚህም ወዲያ አይሁድ ተብለው የሚጠሩ አይሆኑም ፡፡

ጌታችን ድኅነትን ያመጣው ለመላው ዓለም ነው፤ ነገር ግን በንስሐ ከሚመላለሱትና አምነው በምሥጢራቱ አማካይነት በቀናች ፣ በተረዳችና ፣ በጎላች ፣ ሃይማኖት ሆነው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መንገዱን ከሚከተሉት በቀር ድኅነትን የሚያገኛት የለም፡፡

አባት ሆይ ፤ አምነው በንስሐ የሚመላለሱትን ይቅር በላቸው፡፡ በጭፍን ጌታን በመካዳቸው ጸንተው ስለሚገኙ ሰዎች ግን ጌታ «እኔም ወዳለሁበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም» ብሏል፡፡ (ዮሐ ፯፡፴፬) ዳግመኛም እንዲህ ሲል ነገራቸው፤ በኃጢአታቸሁ ትሞታለችሁ ፡፡ እንግዲህ በኃጢአታቸሁ ትሞታላችሁና ፡፡ (ዮሐ ፰፡፳፩-፳፬) በዮሐንስ ወንጌል በስምንተኛው ምዕራፍ ውስጥ ጌታ ሦስት ጊዜ እኔ እንደሆንሁ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ እያለ ነግሯቸዋል፡፡

ይመስሳሉ ብሎ ትንሽም እንኳ ብትሆን ተስፋ ስለሚያደርግባቸው ሰዎች ግን ችላ ቢሉትም ቢያሳድዱትም ቢያሳዝኑትም በዚያው ልክ በቸርነቱ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው የሚለው የመስቀሉ ላይ ቃል እስከዓለም ፍፃሜ ጸንቶ ይኖራል ለምሳሌ እርሱን አንቀበልም በማለት ወደ አገራቸው ጌታ እንዳይገባ ከከለከሉት ወገን መካከል ሳምራውያን አንዱ ናቸው፡፡ በዚህን ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ያዕቆብና ዮሐንስ ለጌታ ቀንተው እሳት ከሰማይ ወርዶ እንድትበላቸው ጌታ ያዝዝ ዘንድ ጠየቁት፡፡ እርሱ ግን ደቀመዛሙርቱን እንዲህ በማለት ገሠጻቸው፤ « ምን ዓይነት መንፈስ እንደሆነላችሁ አታውቁም የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም፡፡ » ( ሉቃ ፱፡፶፪-፶፮) ለደቀመዛሙርቱ የተናገረው ይህን ይሁን እንጂ ስለዚያች ሀገር ግን በልቡ ወደ አብ « አባት ሆይ የሚደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው » ብሎ ሳይጸልዩ አይቀርም፡፡ ስለዚህ እስኪያውቁት እስኪወዱትና እስኪያምኑት ድረስ



www.ethiopianortodox.org

በብዙ መጠባበቅ ታገሳቸው አሁን የምናምን ስለቃልሽ አይደለም እኛ ራሳችን አይተነዋልና እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ እናውቃለን ብለው የምሥራቹን ለነገረቻቸው ሳምራዊት የሚመሰክሩ እስኪሆኑ ድረስ ጠበቃቸው። ( ዮሐ ፬:፵፪)

«**አባት ሆይ ይቅር በላቸው፤**» እኒህ ቃላት ከሁለት የሚበልጥን ፍቅር እና ምሕረት የያዙ ናቸው። ዐቢይነታቸውን በሚገባ ታውቅ ዘንድ እስቲ ሁኔታውን በራስህ እንደሆነ አድርገህ አስበው

አንድ እክል ፈጥሮብህ የነበረን ሰው ይቅር ልትለው ትችላለህ። ግን እስቲ አንድ ሌላ ዓይነት ሰውን ደግሞ አስብ፤ በሐሰት ቢከስህና ያለአግባቡ ቢያስፈርድብህ ሕዝብ እና ሹማምንት በአንተ ላይ እንዲነሣሱ ቢያደርግ፤ ቢሰድብህና ቢዝትብህ እንድትገረፍና እንድትሰቀል ቢያደርግ፤ በእጅህና በእግሮችህ የምስማር ችንካሮች እንዲመቱ ቢያደርግ ....... ይህ ሁሉ ሆኖ ስቃይህ ጫፍ ደርሶ ሳለ ይቅር ትለዋለህ ? ስለእርሱ ትጸልያለህ በደሉ ከክፋት የመነጨ አይደለም ለማለት ለድርጊቱ ምክንያት የምታበጅለት ትሆናለህ እንዲህ ያለውማ ጠባይ ከተፈጥሮ ውጭ የሆነና ተሰምቶ የማይታወቅ ዓይነት ፍቅርን የሚጠይቅ ነው ።

ወደዚህች ሰዓት የደረስሁት ለዚሁ ነውና አባት ሆይ ይቅር በላቸው በሚለው ኃይለ ቃል ብቻ ክርስትና እምነት የመጡ ብዙዎች ናቸው ።

አባት ሆይ ይቅር በላቸው፤ የሚያጽናናኝና ደስታ የሚሆነኝ ይህ ብቻ ነውና። በመስቀል ለተቀበልኩት ሕማም ሽልማቴ ለደረሰብኝ እንግልት ስድብ መከራና ጉስቁልና ሁሉ ካሣ የሚሆነኝ ይህ ነውና ... ሰዎች ኃጢአታቸው አይሎ ገዢ ሆኖባቸው ፣ ለሰይጣን ባርነት ራሳቸውን በማስገዛታቸውና ባላቸው ውስጥ አቅምና ባለማወቃቸው ጭምር እንጂ ይህን ባላደረጉ ነበርና እኔ ላይ እያደረጉ ያሉትን ነገር ዘንግቼ ለእነርሱ አዝንላቸዋለሁ፤ ፍቅር የራሱን አይፈልግምና። ምሕረትህን ይሻሉ ያስፈልጋቸውማል። ይቅርታህ የሚሰጣቸው ከሆነ ተልእኮዬ ፍጻሜን አገኘ ዓላማዬም ተከናወነ ማለት ነው ።

እውነትም ክርስቶስ ስለምን ሰው ሆነ? በደሙ ዋጅቶ እኒህን ይቅር እንዲላቸው ፈልጎ አይደለምን ? በእርግጥም «የባሪያን መልክ ይዞ ፣ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ» (ፊሊ ፪:፯) ምሕረትን እንዲያገኙ ስለፈለገ አይደለምን? ለምን ኃጢአታችንን ተሸከመ?



www.ethiopianortodox.org

በመስቀል እንዲሞት ለምን ተፈረደበት፡፡ የዚህ ሁሉ ዓላማው አንድ ነበር ለእኛ ምሕረትን መስጠት፡፡

ይቅር በላቸው፤ የሚለው ቃል የምሕረት ዘመን መቅረቡን የሚያውጅ ነበር፡፡ ይህ ምሕረት ደግሞ ይሰጣል ተብሎ ቃል ስለተገባለት ብቻ እንዲሁ የተሰጠ ምሕረት አይደለም ፤ ዋጋ የተከፈለበት ምሕረት እንጂ ፡፡ ሰማያዊው ፍትሕ ፍጻሜን እንዳገኘ፣ ቅጣቱም በሙሉ ተከፍሎ እንደተጠናቀቀ የሚያውጅ ቃል ነው ገገርው ከእንግዲህ ዋጋ የከፈለበት ንብረት ባለቤት በራሱ ደም ገዝቶናል፡፡ የቀረውም ነገር ቢኖር ከእርሱ ጋር ሆነን በዘለዓለማዊ ሕይወት ደስ እንድንሰኝና እርሱ ባለበት እኛም ደግሞ በዚያ እንድንሆን እኛን ወደ ሰማያዊው መንግሥት ወደ ገነት መውሰድ ብቻ ነው፡፡

አባት ሆይ ይቅር በላቸው ፤ ከእነዚህ ሰዎች የምትሻው ስለኃጢአታቸው ሞትን ትፈርድባቸው ዘንድ ነውና ክሳቸው ኃጢአት፣ ፍርዳቸውም ሞት ነውና፤ እነሆ እኔ ስለእነርሱ ፋንታ ሞትሁ፡፡ ያለባቸውን ዕዳ ከፍያለሁና ከዚህ ፍርድ ነፃ አድርጋቸው፡፡ እነሆ ሙሉ ዋጋውንም እየከፈልኩህ ነው በቅርቡም ተፈጸመ ብዬ ካሣው መጠናቀቁንም እነግርሃለሁ፡፡

ይቅር በላቸው በሚለው ቃል አማካይነት ጌታችን በሰይጣን ላይ የተቀዳጀውን ድል ያሳውቃል፡፡ ሰይጣን ያደረገው መጣጣር ሁሉ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ለመለየት ፣ ድኅነታቸውን ለማስቀረት፣ ወደ ድኅነት የሚደርጉትን ጉዞም መንገዱን ዘግቶ ለማደናቀፍ ነበር ፡፡ ስለበደላችን የቆሰለው ጌታችን ግን ድንኳኑን በፈሰሰ ደሙ ቀድሶ በማንጻት ያን የተዘጋ መንገድ ከፈተልን ፡፡

የእርሱ ፍቅር የሰውን ጥላቻ አሸነፈ፤ የእርሱ ትሕትናም የሰይጣንን ትዕቢትና ፉከራ ድል አደረገ፡፡ ሕዝቡ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ አሁን ከመስቀሉ ውረድ እያሉት ነበር፡፡ እርሱም አባት ሆይ በማለት በእርግጥ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ገልጾ ተናገረ፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ እያለም ለእነዚያ ሰዎች ይቅርታን ያስገኝላቸው ዘንድ በመስቀል እንደሆነ ቆየ፡፡ ከመስቀል ወርዶ ቢሆን ኖሮ ይቅር በላቸው ለማለት ባልቻለ ነበርና፡፡ መሥዋዕትነትን ያመጣው ፍቅር ይቅርታን የማስገኘት ግዳጅ እንዲፈጽም የሚያስችለው መስቀሉ ብቻ ነበርና፡፡ ይቅር በላቸው



www.ethiopianortodox.org

የሚለው ቃል ከፍጥረት ጊዜ አንሥቶ በተስፋ ሞተው ያለፉ ሁሉ ሊሰሟት የናፈቋት ልመና ናት፡፡ ጌታ ለጠላቶቹና እያሠቃዩት ላሉት እንኳ ያን ያህል ፍቅርና ምሕረት ካለው ለወዳጆቹና ለሚምኑበትማ ያለው ፍቅርና ምሕረት ምን ያህል ይሆን !? ምሕረቱ ምን ያህል ፍጹም ያዘጋጀላቸው ዋጋ ታላቅነትስ ምን ያህል እጅግ ከፍ ያለ ይሆን!?

በመስቀሉ ዙሪያ ግዳጅ ላይ የነበሩት ወታደሮች ይቅር በላቸው የሚለውን ቃል ባደመጡ ጊዜ እጅግ የተደንቀው ነበር፡፡ በቀኙ ተሰቅሎ የነበረውም ወንበዴ እንዲሁ ተደንቆ ነበር፡፡ ለዚሁ ወንበዴ ጌታ ሁለተኛውን ቃሉን ተናገረ፣ «ዛሬ በገነት ከኔ ጋር ትሆናለህ፡፡ »

## ሁለተኛው ቃል

### «እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ፡፡ »

**(ሉቃ ፳፫:፵፫)**

ጌታ በመስቀል ሳለ በመጀመርያ ያነጋገረው ሰው በቀኙ የተሰቀለውን ወንበዴ ነበር፡፡ ይህ ወንበዴ ሕይወቱን ሙሉ እግዚአብሔርን በመፍራት የመራ ሰው አልነበረም፡፡ ለመሰቀል ያበቃውም ኃጢአቱ ነበር፡፡ በመስቀል ሳለ በግራ ከተሰቀለው ወንበዴ ጋር ጌታን ነቅፎ ነበር (ማቴ ፳፯:፵፫)፡፡ ነገር ግን በድንገት ተለወጠና አመነ ፡፡ ጌታን ከመንቀፍ ለጌታ ወደ መከራከር ፣ ከፌዘኛነትም ወደ አማኒነት ፣ በእምነትም የሚጸልይ ሰው ወደ መሆን ተቀየረ ፡፡

ያን እምነት እንዴት አገኘ፤ እንደዚያ ያለውስ መለወጥ እንዴት ሆነለት? ጌታን በክብሩ ሳሆን በሕማሙ አይቶት፤ ብዙዎች ተሰብስበው እተዛባበቱበት ሳለ ተመልክቶት እንደምን በጌታ ለማመን በቃ?

ምንአልባት የዚያን ልበ ደንዳና ወንበዴ ልብ የለወጠው ጌታ ለሚያሰቃዩት ሰዎች ያደረገው ምሕረት ይሆናል፤ በዚህም የእግዚአብሔር ፍቅር እና ቸርነት የዚያን ሰው ጭካኔ ድል አደረገው ልንል እንችላለን፡፡ ምናልባትም የጌታ ሁኔታ በራሱ፤ ገጽታው ደግነት የሚነበብበት አስተያየቱ ነክቶት ይሆናል፡፡ ምናልባትም ጌታ ያን ወንበዴ አይቶት፤ ገና ባየው ጊዜ በአመለካከቱ ብቻ ልቡ ወዲያው ተሰብሮ ፣ ተለውጦ ይሆናል ..... ብቻ የሆነው ምን እንደሆነ ለማወቅ የምንችልበት ምንም ዘዴ የለም፡፡

ምናልባት ወንበዴው ጥንቱንም በውስጡ የንስሐ ዝንባሌ ያለው፤



www.ethiopianortodox.org

መልካም ፍሬን እንዲያስገኝ ከልቡ እሾሁን ነቅሎ ተገቢውን ዘር ዘርቶ የሚያለማውን ገበሬ የሚጠባበቅ ለም መሬት ሆኖ ይሆንን? ይህ ወንጀለኛ በአሥራ አንደናው ወይም በአሥራ ሁለተኛው ሰዓት ወደጌታ ከመጡት ሰዎች ወገን ሆኖ ለመድረስ የበቃ ነው። ጸለየ፤ ጸሎቱም ቅጽበታዊ ምላሽ አገኘ። በብዙ ድካምና ዕንባ ለብዙ ጊዜያት የለመኑና የተማጸኑ ብዙ ሰዎች ነበሩ። ያ ወንበዴ ግን በአንዲት አጭር ቃል አማካይነት ብቻ የሚሻውን ሁሉ አገኘ ። ያቺ የእርሱ ጸሎት ለብዙዎች የመንፈሳዊ ሐሳብና ተመስጦ መነሻ ሆነች። ቤተክርስቲያንም ይህን ጸሎት ከዚህ ሰው ተምራ በጸሎት ቅዳሴ ላይ «**ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ** » አቤቱ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበን በማለት ዘወትር ትጸልያለች።

ጌታ አንዲት ቃል እንኳ ተናግሮ መልስ ሊሰጣቸው ሳይወድ የቀሩ ብዙዎች ሳሉ ያ ወንበዴ ግን ከጌታ ፈጣን ምላሽ ያገኘ ብቸኛው ሰው ሆነ ።

ለፍርድ አቁመውት ሳለ እና ሕማምን በመስቀል ላይ እየተቀበለ በነበረበት ጊዜ ጌታ ብዙዎች ላቀረቡለት ጥያቄ አንዳችም ምላሽ ለመስጠት እንዳልወደደ አስታውስ። ተጨነቀ፣ ተሠቃየ አፉንም አልከፈተም ። ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። ፺ኢሳ ፶፫፡፯) ለሊቀ ካህናቱ ለቀያፋ ብቻ በሕያው እግዚአብሔር አምልሃለሁ ብሎ በለመነው ጊዜ መልስ ሰጥቷል። (ማቴ ፳፯:፲፬) ብዙዎች ተሳለቁበት ነገር ግን መልስ አልሰጣቸውም ሰደቡት የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክስ ከመስቀል ውረድ እያሉ ተፈታተኑት ነገር ግን አልመለሰላቸውም (ማቴ ፳፯:፵) በግራው ተሰቅሎ የነበረው ወንበዴም ክርስቶስ አንተ ከሆንህ ራስህንም እኛንም አድነን ሲል ዘበተበት። ጌታ ግን ምንም አልመለሰም (ሉቃ ፳፫:፴፱) ነገር ግን በቀኙ የነበረው ወንበዴ ገና በመንግሥትህ አሰበኝ ብሎ በተናገረበት ቅጽበት እውነት እልሃለሁ **"ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ"** ብሎ መለሰለት። (ሉቃ ፳፫:፵፪-፵፫)

ጌታ ለዚህ ወንጀለኛ ያሳየው ወዳጅነት እንዴት ደስ የሚያሰኝ ነው። ይህም ወዳጅነት ጌታ በገነትም እንዲቀጥል አደረገ እንጂ በመስቀል ላይ ብቻ እንዲወሰን አልወደደም ። ዛሬ በገነት ትሆናለህ ብሎ ቃል ቢገባለት ብቻ ይበቃ ነበር ነገር ግን «**ከእኔ ጋር ትኖራለህ** » ብሎ ድርብ ቃልኪዳን ሰጠው ።



www.ethiopianortodox.org

በዚያም ያ ወንጀለኛ ከጌታ ወደ ገነት ሲሄድ  አጅቦት የሚጓዝ ጃንደረባ ጌታ ባለበት በዚያ እርሱም ደግሞ እንዲሆን የተፈቀደለት ሆነ፡፡ ይህ ወንበዴ ምንኛ ዕድለኛ ነው ጌታ ወንጀለኛውን ከቶም አልተጸየፈውም፡፡ እንዲያውም በተቃራኒው በውስጡ ቀና መንፈስን አገኘበት በመስቀል ሆኖ ሲያገኘው በዚያ አነጋገረው ወንበዴው ሞትን ከመቅመሱ በፊትም ለወደፊት ድኅነቱ ቃል ኪዳን መተማመኛ ሰጥቶ እርሱን በማስደሰት ጌታም ደስ የሚሰኝ ሆነ ፡፡

በምድር ልብህ ከእኔ ዘንድ ሆኗልና በገነት አንተ ከእኔ ጋር ትሆናለህ በመስቀል ሳለህ ነፍስህን ለእኔ በእምነት አክብረህ  ሰጥተኸኛልና  የወደፊት ዕጣህን  አደራ ያኖርኸው በእኔ ዘንድ ነው፡፡ ከኔ ጋር ሆነህ በመስቀል የተንገላታኸውን ያህል እንዲሁ ከእኔ ጋር ሆነህ ከፍ  ከፍ ትላለህ … አንተ የተሰቃየኸው እኔ ስቃይን በምቀበልበት ወቅት ከእኔ ጋር አብረህ ነውና እንዲሁ ከእኔ ጋር አብረህ በሕይወት ትኖራለህ ፡፡

ይህ በመስቀል የተፈጸመው ግጥምጥም እንዴት ዕፁብ ነው!

በቤተክርስቲያን ሳሉ ከእግዚአብሔር ጋር የተገናኙ ብዙዎች ነበሩ፤ አንዳንዶች ደግሞ ደጃቸውን ዘግተው በመጸለይ ላይ ሳሉ ያገኙታል… ዕጹብ የሆነው ግጥምጥሞሽ ግን በመስቀል ሳለ ጌታን እንዲያገኘው የሆነለት ሰው ነው ወንበዴው አንድ ቀን ተጸጽቼ ወደ እግዚአብሔር እመለሳለሁ ብሎ አስቦ የሚያውቅ ቢሆን ፤ያ መመለስና እግዚአብሔር ማግኘት የሚፈጸመው በዚያች ሥፍራ ሊሆን ይችላል ብሎ አስቦ ያውቅ ይሆን?

በእርግጥም የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም (ሉቃ ፲፯:፳) ፡፡ በአንድ ሰው ላይ ጸጋ እግዚአብሔር መቼና እንዴት ሥራውን እንደሚሠራ የምናውቅበት መንገድ የለም፡፡

እውነትም ነፍስ ወደሚወደው (ወደሚሻበት) ይነፍሳል (ዮሐ ፫:፰)፡፡ ይህ ወንጀለኛ  ሕገ ወጥነትና ኃጢአት የተመላበትን ሕይወት አሳልፏል ፡፡ በመስቀል ሰላም ከነኃጢአቱ የነበረ ከመሆኑም በላይ በግራ ከተሰቀለው ወንበዴ ጋር አብሮ ጌታን ነቅፏል፡፡ ነገር ግን ጸጋ እግዚአብሔር ተነፈገው? በእግዚአብሔርስ ለዘለዓለም የተረሳ የተተወ ሆነን? እንደውም በተቃራኒው ጸጋ እግዚአብሔር ወደ እርሱ ሄዶ ሥራን የሚያከናውንባትን ትክክለኛ ሰዓት በመጠባበቅ ላይ ነበር፡፡ ከዚያም ከሞት አፍታ ያህል ብቻ ርቆ ባለባት በዚያች ደቂቃ የድኅነት ሰዓት መጣችለት ፡፡

ማን በእግዚአብሔር እንደሚመረጥ የምናውቅበት አንድም መንገድ



www.ethiopianortodox.org

የለም። አሁን ይህ ወንበዴ ይመረጣል ብሎ ማን ጠረጠረ ? ማን አሰበ? ሌሎች በአሥር የሚቆጠሩ ዓመታትን የፈጀ ብዙ ድካምን እንዲከፍሉ የሆነባት ነገር ለዚህ ሰው በአንዲት ሰዓት ብቻ ይፈጸምለታል ብሎ ማን ገመተ ? እኛስ ሰው ነንና ላይ ላዩን ያለ (የሚታይ ) ሁኔታን ተመልክተን እንዳኛለን። አንዳንዶቹን እንንቃለን ለአንዳንዶችም እናዝንላቸዋለን። ነገር ግን ከምንንቃቸውና ከምናዝንላቸው መሀል ማንኛውም ሰው ቢሆን ይሄን ከእኛ እጅግ የተሻለ የሚባልለትም ሰው ይሆናል። ነገር ግን ይህ ወንበዴ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደሚገባ የተገባው እንደሆነ እናምንበታለን።

በዚያች ሥፍራ በዚያች ሰዓት ባደረገው ነገር ሁሉ እጅግ ግሩም እጅግ ድንቅ ሰው ነበር። ይኸ ወንበዴ ጌታ ሆይ ብሎ በተናገረ ጊዜ የጌታን ጌትነት አመነ (መሰከረ)።

ወደ ገነት ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊያስገባኝ የሚቻለው ነው ብሎ በማመኑም ጌታን በአዳኝነት አመነ (አዳኝነቱንም ተናገረ)።

በመስቀል ሳለ ይህ ወንበዴ የራሱን ኃጢአት ተናዘዘ፣ ሞት የሚገባው እንደሆነ አምኖም ተናገረ። በግራ የተሰቀለውንም ወንበዴ እንዲህ ሲል ገሰፀው፤ **ስለአደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለን በእኛስ የተደረገው እውነተኛ ፍርድ ነው** (ሉቃ ፳፫:፵፵-፵፩) አመነ መሰከረ ስንልም ጌታ ያለኃጢአቱ መስቀሉን አመነ ማለት ነው። ይህ ደግሞ ስለሌሎች ኃጢአት የተሰቀለ መሆኑን ማመን ነው።

ከዚህ ሁሉ ሕዝብ መካከል ለጌታ የተከራከረለት አንድ ሰው ቢኖር ይህ ወንጀለኛ ሰው መሆኑ እጅግ የሚደንቅ ነው። ከአስራ ሁለቱ ሐዋርያትም በእርሱ ከተፈወሱ ብዙዎች መካከል ለእርሱ የተከራከረለት ስድብም አይገባውም ብሎ የተናገረው በቀኙ የተሰቀለው ወንበዴ ብቻ ነበር። ከሐዋርያትና ከምዕመናን ወገን የጌታን ነገር ዓላማ ብሎ ይዞ የሚከራከረው ሰው አንድ ሌባ (ወንጀለኛ) ነው የሚሆነው ብሎ ለማሰብ የቻለ ኖሮ ይሆን ?! በእርግጥም ጌታ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ ያለው ቃል ምንኛ የተገባ ነው (ማቴ ፲:፲፰) ወንድሜ የራስህን እርባና በአንተ አግዝፈህ አትገምት፣ እንዲህ ካሉ ሰዎች የተሻልኩ ነኝ ብለህ አታስብ፤ የተሻልክ የሆነህ መስሎም አይሰማህ። ከሐዋርያትም ሆነ ከጌታ የቅርብ ተከታዮች ወገን ከአንዱም ጋር እንኳ እኩል ነኝ ብለህ ከቶም አታስብ አትገምት። እኒያ ሁሉ በመስቀሉ ሰዓት ገለል አሉ፤ ለጌታ ሊከራከሩም



www.ethiopianortodox.org

አልቀረቡም። ለጌታ የተከራከረለት ቢኖር ቀማኛው ሰው ነው። ይሆናል ተብሎ ከቶም ያልተጠበቀ ፈጽሞም የማይታወቅ ግለሰብ ለጌታ ከመከራከሩም ውጪ ስለዚህ ወንበዴ ሌላው ደስ የሚያሰኝ ነገር ደግሞ ስለ ዘለዓለማዊ ሕይወቱ በማሰብ ተጠምዶ የነበረ መሆኑ ነው ። ለማያልፈው ዓለም ራሱን ለማዘጋጀት ተጣደፈ። እንደ ጌታችን እርሱም በአካሉ እየተሰማው ስለነበው ሕመም አልተጨነቀም ፤ ስለ ዘለዓለማዊ ሕይወቱ እንጂ ስለዚህም ፍጹም በሆነ ንስሐና ጸሎት ጌታ ሆይ አስበኝ ሲል ለመነ። በኃጢአቱ ሳይሆን በጸጋህ አስበኝ ።

«አቤቱ ምሕረትህንና ቸርነትህን አስብ ከጥንት ጀምሮ ናቸውና የልጅነቴን ኃጢዓትና መተላለፍ አታስብብኝ ። አቤቱ ስለቸርነትህ ብዛት እንደ ምሕረትህ አስበኝ።» (መዝ ፳፬(፳፭)፡፮-፯) አስበኝ! አላውቃችሁም ብለህ ከተናገርሃቸው ወገን እንዳትቆጥረኝ አስበኝ። በዚህ የነበረንን አብሮነት አስብ፤ ከሕይወቴ ጊዜያት ሁሉ በመስቀል ከአንተ አጠገብ ያሳለፍኳቸው ጥቂት ሰዓታት እጅግ ዋጋ ያላቸው እነርሱ ናቸው። በሕማምህ ጊዜ አብሬ የተገኘሁ መሆኔ ደስ አሰኝቶኛል። ከአሁን ወዲያም በክራት ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ ብዬ ለመናገር እችላለሁ። (ገላ ፪፡፳)

ስለዚህ አብሮነታችን ብለህ አስበኝ! መቼም የእኔ ከአንተ አጠገብ ሆኖ መሰቀል ለአንተ የሚያሳፍር ነገር ሊሆን የሚገባው ነው። ለእኔ ግን የዘለዓለም መመኪያ የሚሆነኝ ነገር ነው። እነኚህ ከአንተ አጠገብ ያሳለፍኳቸው ጥቂት ሰዓታት ብቻቸውን የሚበቁኝ ናቸው ነገር ግን ደግሞ በዚያው ከምወሰን ይልቅ እነኚህ ሰዓታት ለዘለዓለማዊ ወዳጅነታችን መነሻ ብቻ ቢሆኑልኝ ፤ እንጂ ከአሁን ወዲያ የማይደገሙ ትዝታዎች ሆነው ባይቀሩብኝ እንዴት አወደድሁ!

አስበኝ የሚለው ቃል ተናጋሪው ከአድማጩ ጋር አቀድሞ የሚተዋወቅ ወዳጅነት የነበረው ሰው እንደሆነ የሚጠቁም (የሚያሳይ) ነው። አስቀድመህም ታውቀኛለህ በመዝገብህ የተጻፍኩ በመጻፍሕም የተቀረጽሁ ነኝ. . . የሚል መልዕክት አለው ።

ጌታ ሆይ ከአመፀኞች ጋር ተቆጠርህ (ኢሳ ፶፫፡፲፪) ከኃጢአተኛዎችም ጋር ተሠቀልህ። ይህ ለአንተ የሚያዋርድ ነገር ሆኖ ሳለ ለእኔ ግን የጸጋና የደስታ ምንጭ ሆነኝ። በአጠገብህ መሆን እንዴት መልካም ነው ሕመሜን ሁሉ ያቀልልኛል። እንደውም መንፈስህ ሰውነቴን ሁሉ ሲያጠራው



www.ethiopianortodox.org

ሲያነባውና ሲቀድሰው ፤ እኔንም አዲስ ፍጥረት አድርጎ ሲያዘጋጀኝ ሲቀይረኝ ይሰማኛል እንጂ ሕመም የሚባል ነገር አይሰማኝም ። የፀሐይ ጨረር ቆሻሻ ላይ ቢያርፍ ቆሻሻውን ቢያጠራ እንጂ ቆሻሻው ጨረሩን አያሳድፈውም ፤ አንተም እንደዚያች ጨረር ነህ ። ሳይገባኝ ወዳጅነትህን የምከጅል ነኝ። ቀድሜ ባወቅሁህ ኖሮ መልካም ነበር። ስለዚህ አስበኝ ።

እኛ ሁላችን ከዚህ ወንበዴ ጋር አስበኝ የሚል ልቦና ቢኖረን ምንኛ እወድ ነበር። በሩቅ ሀገር ከቤትህ ተለይቶ የሄደ ብኩን ባርያ የሆነ ልጅ እንዳለህ አስብ። ከወደቅሁበት ታነሳኝና መንፈሴንም አርነት ታወጣው ዘንድ ደካማነቴን እና የተዋረድሁ መሆኔን የሰይጣን እስራት የፀናብኝ እና የወደቅሁ እንደሆንሁ ይህን አሰብ። ሌላ የሚያስብኝ ማንም የለኝምና አስበኝ። ውሃው በተናወጠ ጊዜ ጌታ ሆይ በመጠመቂያይቱ ውስጥ የሚኖረኝ ሰው የለኝም። (ዮሐ ፭፡፯)።

የዚህ ወንበዴ ታሪክ ሰዎች ለሞት በተቃረቡበት ሰዓት በሚያደርጉት ድርጊት እንደሚለያዩ ያሳየናል። በቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ ከመሞቱ ጥቂት አስቀድሞ ጌታን አስበ ፣ ተፀፀተም። በተቃራኒው በግራ የተሰቀለውም ወንበዴ እንደዚያኛው ለሞት ተቃርቦ ሳለ ጌታን እየነቀፉ ነበር። እግዚአብሔርን ከቶም አልፈራም ስለዘለዓለማዊ ሕይወቱም ጥቂት እንኳ ግድ አልነበረውም እርሱን ያሳስበው የነበረው የቀደመ ብኩን ሕይወቱን ለመቀጠል እንዲችል እንዴት ከዚያ መስቀል ለመላቀቅ እንደሚችል ብቻ ነበር። (ሉቃ ፳፫፡፴፱ ) በዚያም ሁኔታ ሳለ ኀደኛው ፈያታዊ ዘየማን ወቀሰው። በዚያች ለሞት በተቃረበበት ሰዓት እንደቀደመው ያለ አንዳች ቅሬታ ጥፋትን በመሥራቱ ገፋበት እንጂ አንዳችም የፀፀት መንፈስ አልነበረውም። በአካላዊ ርቀትና ቅርበት በኩል በግራ የተሰቀለው ወንበዴ በቀኙ እንደተሰቀለው ወንበዴ ከጌታ አጠገብ እዚያው ቅርቡ ነበር። የሞት ሰዓት ንስሐን እንዲያስባት ያለበትንም ሁኔታ እንዲመረምር አላደረገውም።

ጌታ ለሚያሰቃዩት ሰዎች ያደረገው ምሕረት ወደ ልቡ ከቶም አልገባም ምንም አልመሰለውም፤ ሌላው ቀርቶ ኀደኛው ፈያታዊ ዘየማን ወደገነት እንዲገባ ቃል ኪዳን መቀበሉ እንኳ ቅንዓት ጉጉት እንዲያድርበት አላረገውም። ምድር ስትነዋወጽ ዓለቶች ሲሰነጣጠቁና ጨለማ በዚያች ሥፍራ ሲነግሥ ያኔ እንኳ አላሳመነውም። አሁንም በዓለም ፍቅር እና ምድራዊውን



www.ethiopianortodox.org

ሕይወት ለመቀጠል በሚፈልግ ምኞት እንደተያዘ ነበር፡፡ ከመስቀል እንዲወርድ እንዲረዳው እንጂ ከዚያ ውጪ ከጌታ ወዳጅነቱንም ሆነ አብሮነቱን አንድም አልፈለገም፡፡

የሕይወታቸው ማብቂያ መቼ እንደምትደርስ ፈጽሞ ሳያውቁ ንስሐ ሳይገቡ ፣ ስሸመግል እያሉ ለሚያዘገዩ ሰዎች ይህ ታሪክ ትልቅ ትምህርት አለው፡፡ ብዙዎች ለሞት ቀርበው ሳሉ ጠባያቸው እንደፈያታዊ ዘፀጋም ይሆናል፡፡ እየተራገሙ እያመጹና ምድራዊውን ሕይወት ላለመላቀቅ ሙጥኝ ብለው እያስቸገሩ ያልፋሉ፡፡ ልማድ የተዋሐደው ሰው በሰውነቱ ጦር ቢወደርበትና ነፍሱን አሳልፎ የሚሰጥባት መስመር ብታቀርብም እንኳ ያን ማድረግ አይበጀኝም ብሎ ለመጣል ያቅተዋል፡፡ ሰው ለእግዚአብሔር አጸፋዊ ምላሽ ካልሰጠ በሞት ሰዓት እንኳ ኃጢአት ሊሠራ ይችላል ፡፡

ንስሐን ሽተው ሳይሆን ሞት በዚህ ዓለም ከሚወዱት ነገር ስለሚለያቸው ብቻ ለሞት ሲቃረቡ አምርረው የሚያለቅሱ ሰዎች ብዙ ናቸው፡፡ ሞት ከሚወዷቸው ሰዎችና ከምኞታቸው ቆርጦ ስለሚለያቸው ያለቅሳሉ፡፡ በዚያች በሞት ሰዓት እንኳ ዓለም የምታጓጓ ሆና ነው የምትታያቸው፡፡ ሞት ሰውን የግድ እጁን ወደ መስጠት በጄ ብሎ ወደመገዛት ያመጣዋል ብለህ አታስብ፡፡ ለአንዳንዶች እንጂ ለሁሉም የሚሠራ አካሄድ አይደለም፡፡ የሞትን ሰዓት በቀኝ የተሰቀለው ተጠቀመባት፣ በግራ ተሰቀለው ወንበዴ ጌታን በመዝለፍና በጌታ ላይ በመዘባበቱ ሲገፋበት ኀደኛው ፈያታዊ ዘየማን ግን **«በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ** » እያለ ለመነ፡፡

ጌታ በፀፀት የነበረውን ይኸን ወንበዴ ችላ አላለውም፡፡ ለጸሎት ምላሽ ለመስጠት እንኳ አላመነታም፡፡ ወንበዴው ከጠበቀው ይልቅ በፈጠነ ቅጽበት ምላሽ አገኘ፡፡ በማትቀረው በሞት ሰዓት ሆኖ ጌታ ምሕረት አያደርግልኝም ብሎ አልሰጋም ተስፋም አልቆረጠም፡፡ ጌታም በበኩሉ **«እውነት እልሃለሁ ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ** » ሲል ምሕረቱን አረጋገጠለት አፀናለት፡፡

አሁን ከእኔ ጋር ነህ ፤ ከአፍታ በኋላም ደግሞ ከእኔ ጋ ነህ፤ ነገር ግን በሁለቱ የአብሮነት ጊዜያት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ በስቃይ ጊዜያት ከእኔ ጋር እንደነበርህ በገነት ደግሞ ከእኔ ጋር ትሆናለህ፡፡ ከዚህ ሕማምን ትቀበላለህ ፤ እዚያ መጽናናትን ታገኛለህ

ጌታ በገነት ብሎ ሲናገር ወንበዴውን እያረመው ነበር፡፡ ወንበዴው



www.ethiopianortodox.org

**«በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ** » ብሎ ለመነ፡፡ ጌታ በሰማያት መንፈሳዊ መንግሥት እንዳለው፤ በዚህ ዓለም ያልሆነች እንደሆነች አምኖ ነበር፡፡ ሰዎች ግን ወደዚያች መንግሥት ከፍርድ ቀን በኋላ እንጂ በፊት ለመግባት አይችሉም፡፡ ከሞት በኋላስ ሰዎች ወደ መቆያ ሥፍራ ይሄዳሉ የሚያምኑና ታምነው የተገኙ ሰዎች እስከ ፍርድ ቀን የሚቆዩበት ሥፍራ ገነት ነች፡፡ ስለዚሁ ጌታ ለወንበዴው ዛሬ በሰማያዊት መንግሥቴ ትሆናለህ ብሎ አልመለሰለትም፡፡ **«በገነት»** ትሆናለህ ብሎ አለው እንጂ፡፡ በገነት ብሎ በማረምም የእውነተኛ መምህርነት ሥራውን አከናወነ በመስቀል እያለም እንኳ የደገኛ መምህርነት ተግባሩ አልተቋረጠም፡፡ ጥፋትን ለአጥፊው ያለ ቁጣና ነቀፋ የሚጠቁም መምህር ነውና፡፡

**«በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ** » . . .. ይህ ቃልኪዳን ነው፡፡ ዳግም በምመጣበት ጊዜም እንዲሁ ከእኔ ጋር ትመጣለህ፡፡ አሁን በመስቀል በቀኜ እንዳለህ በፍርድ ቀንም በቀኜ ትቆማለህ፡፡ ጻድቃንን የምትወክል ትሆናለህ በመንግሥቴ ከእኔ ጋር ትሆናለህ በዘለዓለማዊ ሕይወትም እንዲሁ እነሆ እኔ ለዘወትር ከአንተ ጋር ነኝ፡፡

ይህ ቃል ኪዳን ይህ ከጌታ ጋር እሆናለሁ የሚል ጉጉት እና መጠባበቅ ምናልባት ይህ ወንበዴ ሞትን በደስታ እንዲቀበለው አድርጎት ይሆናል፡፡ ሞት እንዴት መልካም ነው! ብሎ ለመናገር ያስደፍራል፡፡ ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ሞት ኃጥአንን ያስፈራቸዋል ያስጋቸዋል፡፡ ጌታ ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ ብሎ ያጽናናቸው ዘለዓለማዊ ሕይወትና አክሊል እንደሚጠብቃቸው ተስፋ የተሰጣቸውና በተስፋ ሆነው የሚሞቱ ግን ሞት ለእነርሱ የደስታቸው ምንጭ ነው፡፡

ጌታ « **በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ** » ብሎ በተናገረው ጊዜ ወንበዴው ለኃጢአቱ ምሕረት ፣ ሥርየት እንደተሰጠው የነገረው ብቻ አይደለም ፤ ከአዳም በኋላ ተዘግታ የነበረችው ገነት በአዳም ኃጢአት ምክንያት የሰው ነፍስ ሊደርስበት የማይችልበት ሥፍራ ነበረችና፡፡ ስለዚህም ነገር ከምዕመናን ወገን አንዱ በሞት በሚለይ ጊዜ ቤተክርስቲያን «ለፈያታዊ ዘየማን እንዳደረግህለት እንዲሁ ለዚህች ነፍስ የገነትን ደጆች ክፈትላት» ስትል ትጸልያለች ፡፡ ለወንበዴው ምሕረት መሠረቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ የገነትም ደጆች መከፈት ሰማያዊ



www.ethiopianortodox.org

ድንቅ ነው፡፡ እነዚህ ጌታ በመስቀል ሆኖ ያከናወናቸው ተግባራት የእርሱን ሰማያዊ አምላክነት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ጌታችን ወንበዴው ምሕረትን ያገኝ ዘንድና በገነት ይሆን ዘንድ የለመነ አይደለም፤ ያዘዘ የፈቀደም እንጂ፡፡ ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ ሲለው የሰውን ዘለዓለማዊ ሕይወት በተመለከተ የሚፈርድበትን የጻድቅ ፈራጅነት ሚና ስፍራ እንደያዘ ሆኖ ነው፡፡ በመስቀል የነበረ ሆኖም ሳለ ጽድቅ ፈራጅ አምላክ ነበረና ወንበዴው በዚያኑ ዕለት ወደገነት እንዲገባ ወሰነ፡፡ ከሰው ወገን ይህን ለማድረግ የሚቻለው አለን? ይህ በሰው ሊከወን የማይችል የእርሱ ብቻ የሆነ ሰማያዊ ሥልጣን ሰማያዊ ተግባር ነው የገነት ደጆችንም መክፈት ሊቀ ካህንም ቢሆን ነቢይም ቢሆን ከሰው ወገን በማንም ሊፈጸም የማይችል ሰማያዊ ሥልጣን ነው፡፡ እኒህ ሁሉ ሰዎች መድኅን ያቺን ደጅ እስኪከፍታት ሲጠብቁ ኖሩ፤ እርሷን መክፈት ሰማያዊ ሥልጣን ነበርና፡፡ የገነት ደጆች መከፈት ስለዚሁ ነገር ለእኛ የፈሰሰው ደም በቂ ዋጋ እንደሆነ ጭምር የሚያሳየን ነው፡፡

በእውነትም ኃይልና ሥልጣን ያለው እርሱ ነው «የሚከፍት፤ የሚዘጋም የሌለ፡፡ የሚዘጋ፤ የሚከፍትም የሌለ፡፡ » (ራዕ ፫:፯ ፤ኢሳ ፳፪:፳፪) ሞትና የገሀነም መክፈቻ በእጁ ነው፡፡ ለደቀመዛሙርቱና በምድር ላሉ ተከታዮቹም ይህንን ቁልፍ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡ ለልባሞቹ ደናግል ደጃፉን የከፈተላቸው እርሱን ለመኑ (ማቴ ፳፭:፲፩) ሆኖም ግን ለእርሱ ለታመኑት ካልሆነ በቀር የገነትንም ደጅ ለልላ ለማንም አይከፈትም ፡፡ በእርሱ መታመን እንደ ወንበዴው ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትለሆናለህ የሚለውን ቃል ለመስማት ያበቃል ፡፡

«ዛሬ» የሚለው ቃል (ካቶሊኮች) እንደሚያምኑት ነፍስ ወደገነት ከመግባቷ አስቀድሞ እስክትነፃ የምትቆይበት ሥፍራ እንደሌለ ያለጥርጥር ያረጋግጣል፡፡ ወንበዴው ወደገነት የገባው በሞተበት ቀን እንጂ ለአንዲት ሰዓት እንኳ እስኪነጻ የሚቆይበት ሥፍራ እንዲወስድ አልሆነም ዛሬ የሚለው ቃል ሙታን ካረፉበት ቀን አንሥቶ እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ መንፈሳቸው በሞተው ሰው ቤት እየመጣ ወዲያ ወዲህ ይላል፤ አንድ መላ ካልተበጀም (በቅዳሴ ጊዜ ስሙ ካልተጠራ) ይህ መንፈስ ከዚያ ሥፍራ አይርቅም የሚባል፡፡ አፈታሪክ (አጉል እምነትን)



www.ethiopianortodox.org

ድል የሚነሳ (የሚረታ) ነው ። የወንበዴው ነፍስ እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ እዚሁ ቆየች ወይስ ዕለቱን ወደገነት ገባች? መልሱ ግልጽ ነው።

«ገነት» በሚለው ቃሉ ጌታ ሰዎች ከሞት በኃላ የሚሄዱበትን ሥፍራ አመለከተ። ታምነው የተገኙ ሁሉ የሚቆዩበት እና እስከ ፍርድ ቀን ድረስም ከጌታ ጋር ሆነው ደስ የሚሰኙበት ሥፍራ እርሷ እንደሆነች ያስረዳል።

«ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናል » የሚለውን ቃል እስኪ በተመስጦ እንመርምረው። ከጌታ ጋር መሆን ይበልጥ ደስ የሚያሰኝ ነው። ወይስ በሌላ አነጋገር በገነት ከምናገኘው ነገር ሁሉ በጣም ደስ የሚያሰኘውና የሚልቀው ከጌታ ጋር በአንድነት መሆን ነው። ጌታ ደግሞ ቃል የገባልን ይህንኑ ነው። እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ፤ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ። (ዮሐ 14-3)

ይህ እንዴት ግሩም የሆነ ቃል ኪዳን ነው! ልዩ በሆነ ስሜት የምንደክምለት ግባችንና ተስፋችንም ይኸው ነው ..........

ምፈሳዊ ሕይወታችን ባጠቃላይ ከጌታ ጋር ያለን ሕብረት (አንድነት) ኑሮ ነው።

በዚህ ቃል ኪዳኑ ጌታ ወንበዴውን ደስ አሰኘው ። በመስቀል በአካሉ እየደረሰበት ያለው ሕማም እንደዚያ የከፋ ሆኖ ሳለ እንኳ ጌታ ወንበዴውን ለማረጋጋት ለማነጋገር እና ለማስደት ይህን አከናወነ። በእሾህ፣ በችንካር፣በጦርና በግርፋት የደረሰበትን ሕማም ሁሉ ዘነጋው ። የወንበዴውን ቃል በሚገባ አዳመጠው፣አነጋገረው አረጋጋው -በእርግጥም ፍቅር የራሱን አይፈልግም (፩ ቆሮ ፲፫፡፭) ብዙ ጊዜ በሥራና በጉዳዮች ተጠምደን ሳለን ሰዎች አንዳች ሽተው ወደ እኛ ይመጣሉ። ወደ እኛም በመምጣታቸው እንማረራለን እንነገሽገሻለንም። ለእነርሱ የሚሆን ጊዜ እንደሌለንና በሌላ ጊዜ እንዲመለሱ ነገረን እናሰናብታቸዋለን ። እስቲ ጌታን አስቡት። በመስቀል ሆኖ ሳለ እንኳን እንዲህ ያለውን ቃል አልተናገረም ። ሕማም ላይ እያለ ሆኖ ሳለ እንኳ ለወንበዴው ጆሮውን አልነፈገውም። ወንበዴው የፈለገውን ትኩረት አዳማጭ ጆሮ ሰጠው፤ ለልመናው ምላሽን ሰጠው፤ ልቦናውን ደስ አሰኘው። በዚህም ለእኛ በመስቀል ሆነንም እንኳ ለሌሎች ችግር መድረስ፣መጠገን፣መሙላት የሚቻለን እንደሆነ በተግባር አሳየን። ጌታ ለወንበዴው በሰጠው ትኩረት



www.ethiopianortodox.org

ለአንድ ግለሰብ የሚሰጥ ትኩረት ለቡድን ለብዙ ሰዎች የሚሰጥ ትኩረትን ይህል ዐቢይ እና አስፈላጊ እንደሆነም አሳይቶናል ። ለመላው ዓለምና ለእያንዳንዱ ምዕመን ካደረገው የመሥዋዕትነት ተግባር ሌላ ለሚያንገላቱት ሰዎች ካደረገው ምሕረት በተጨማሪ የግለሰብንም ጉዳት ደግሞ ጠግኗል የወንበዴውን። በጌታ ዘንድ አንድ ግለሰብ የአንድን ቡድን ወይም ብዙ ሕዝብ ያህል የመጎብኘት፤ ክብካቤን ማግኘት ትኩረትን የመሻት መብት አለውና። አንድ ግለሰብ የብዙ ሕዝብን ያህል ዐቢይ የሆነ ዋጋ ረብ ወይም ጥቅም አለው።

ጌታ ወንጌልን በሚያስተምር ጊዜ በግልም በሕብረትም እንደነበረም ደግሞ እንረዳለን ። በተራራው ስብከቱ እና በአምስት ዳቦና በሁለት ዓሣዎች በመገባቸው ብዙ ሺህ ሰዎች መካከል ሳለ ለብዙዎች አስተማረ ብዙዎቹን ጎበኘ። በተመሳሳዩ ከአሥራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት ጋር ወይም ከጴጥሮስ ከያዕቆብና ከዮሐንስ ጋር በነበረ ጊዜ ወይም ከኒቆዲሞስ ጋር፣ ከማርያምና ከማርታ ጋር በቤታቸው፤ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር በውሃው አስተምሯል። ግለሰቦችን ጎብኝቷል።

እግዚአብሔር ከብዙዎቹ መካከል ያለ አንድን ግለሰብ አይዘነጋም ። ከዘጠና ዘጠኝ በጎች መሃል አንዱ ቢጠፋ በዘጠና ዘጠኙ በጎች ምክንያት ያ የጠፋው አንድ በግ ጠፍቶ፣ተዘንግቶ አይቀርም። የዓለም ሁሉ የመዳን ጉዳይ ያለ ቢሆንም የወንበዴው ነፍስ ጉዳይም የሚዘነጋ፣ የሚጠፋ አይሆንም።

## ሦስተኛው ቃል

### «አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ . . .እናትህ እነኋት»

**(ዮሐ ፩፱ ፡ ፳፮-፳፯)**

አስቀድመን እንደገለጽነው ጌታ በመስቀል ሳለ ያሰበው ጉዳይ የሌሎች ሰዎች ነገር ነበር። ያሰቃዩት ስለነበሩት ሰዎች ለአብ «አባት ሆይ ይቅር በላቸው» ሲል ጸለየ። በቀኙ ለተሰቀለው ወንበዴም አስቦ «ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ» አለ። ከዚያም ትኩረቱን ወደ እናቱ አደረገና ለሚወደው ደቀመዝሙሩ ለዮሐንስ አደራ ሰጠው ።

ለእናቱ "**እነሆ ልጅሽ አላት ፤ ለዮሐንስ እነኋት እናትህ** አለው። «ከዚያም ሰዓት ጀምሮ ደቀመዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት።» (፩ኛ ዮሐ



www.ethiopianortodox.org

፱:፳፯)

በዚህም ጌታችን ለቤተሰቦቻችን በተለይም ለእናቶቻችን ክብካቤ ማድረግ እንደሚገባን አርአያ ሆኖ አሳየን። ዘጠኝ ወር ማደሪያው ለነበረችው በሕፃንነቱ ተከባክባ ላሳደገችውና እርሱም ይታዘዛት ለነበረችው እናቱ አሰበላት። (ሉቃ ፪:፶፩) በተለምዶ ሕማም ላይ ያለ ሰው ከሌሎች ትኩረትን፣ ክብካቤን ያገኛል። ጌታ ግን በሕማሙ ሳለ ለሌሎች ትኩረትና ጥበቃን የሚያደርግ ነበር። አሁንማ በክብሩ ሆኖ ለእኛ ያለው ጥበቃ ምን ይልቅ!

ትኩረቱን በመጀመርያ ኃጢአትን ይቅር ወደ ማለት አደረገ፤ ከዚያ ደግሞ አብሯቸው ለኖራቸው ወደ ማሰብ። ከነዚህም ወገን የመጀመሪያዋ ተጠቃሽ ክብርት እናቱ ነበረች።

ጌታ በመንፈሳዊ ተልዕኮ ለሚራዱት በማሰብ ትኩረቱንም ወደነሱ በማድረግ የቤተሰቡን ጉዳይ ችላ እንዳለና ቤተሰቤ ብሎ እንደማያያቸው አድርገው የሚያምኑ እንዳንዶች አሉ። ይህም በማቴዎስ ወንጌል ፲፪፡ ፵ ፡-፳፱ የተጻፈውን ቃል በተሳሳተ መልኩ በመረዳት ነው ። ቃሉ እንዲህ ይላል ፤ «እናቴ ማን ነች?» ወንድሞቼስ እነማን ናቸው ? በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደረግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ እህቴም እናቴም ነውና። ጌታ በመስቀሉ ለእናቱ በተናገረው ቃል ቤተሰቡን በቤተሰብነት አላያቸውም የሚለውን የተሳሳተ ትርጓሜ ረትቷል።

ለእግዚአብሔርና ለአንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያን ራስንና ሕይወትን መስጠት ማለት ሰው በዚያ ምክንያት ወገኖቹን በተለይም ደግሞ ቤተሰቡን ችላ ይላል ማለት አይደለም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ነገር ግን ለእርሱ ስለሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖቱን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው። (፩ ጢሞ ፭:፰) ለአገልግሎት ራስን መስጠት አንድ ሰው ቤተሰቡን በተለይም ደግሞ እናቱን እንዳያገለግል እንዳይጠብቅ ሰበብ ምክንያት ሊሆን የሚችል ነገር አይደለም ።

ጌታችን እና ቅድስት እናቱ የመገናኘታቸውና መለያየታቸው ነገር በዚህ መልኩ እንደሆነ አስቀድሞ የተወሰነለት ይመስላል። ጌታ ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ በመጀመሪያ ያየው መልክ የእርሷን የተቀደሰ ገጽ



www.ethiopianortodox.org

ነበር፡፡ ነፍሱን ለአብ አደራ ከመስጠቱ በፊትም በመጨረሻ ያየውም እንዲሁ የእርሷን ገጽ ነበር፡፡ ልጅዋ በሄደበት ሁሉ ትከትለው የነበረችና በሕማሙ ጊዜ ጥልቅ በሆነ ፍቅርና ኃዘን በመስቀሉ እግር ሥር ቆማ የነበረች እናት ናት ፡፡

በዚያም ሳለች ልጄና አምላኬ ሆይ፣ ዓለም ድኅነትን በመረከቡ ሐሴት ያደርጋል እኔ ግን ለሰው ሁሉ በኀነት ስትል በትዕግስት የተቀበልከውን ስቅለትህንና ሕማምህን ስመለከት ልቤ በውስጤ እጅግ ይቃጠልብኛል - እያለች እንዲህ በመሳሰለው በሚስደንቅ ቃል ትናገር ነበር፡፡ እርሱም እናቱን እንደሚወድ ልጅ በሕማም ሳለ እንኳን የእናቱን አደራ ሥፍራ አስያዘ ፡፡

ስለዚህ ጌታ በሐዘኗ ያረጋጋት ዘንድ በትካዜዋ ጊዜ ጥበቃ ክብካቤ ያደርግላት ዘንድ እንደሚገባው አሰበ፡፡ «**በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል** » ተብሎ የተነገረለት ሐዘን ደርሶ ነበርና (ሉቃ ፪:፴፭) ልጇ እንደመሆኑ እናቱን በሐዘኗ ማረጋጋት እንደሚገባው አሰበ፡፡ እርሰዋን በማነጋገር አኳኋኗን አብሯት የሚሆን መንፈሳዊ ልጅንም በመስጠት አጽናናት፡፡

ጌታ በመስቀል ሳለ ለእናቱ የተናገረው ቃል በቀኙ ከተሰቀለው ወንበዴ ጋር ከተለዋወጠው ቃል የተለየ ነበር፡፡ ወንበዴው ቀድሞ አናግሮት ጌታ ለዚያ መልስ ሰጠው ፡፡

ለቅድስት እናቱ ግን ቀድሞ ያናገራት ጌታ ነው፡፡ እርስዋ እስክትናገር ድረስ አልጠበቀም፡፡ ሐዘኗን ገልጻ እስክትናገር አልጠበቀም፡፡ ነገርግን በልብዋ ይዛ መጠበቅ (ዝም ማለት) በሕይወቷ የለመደችው ነገር ነበርና (ሉቃ ፪:፲፱) እንዲህ ይደረግልኝ ብላ የእርስዋን ነገር ጥያቄ የምታቀርብ አልነበረችም፡፡ በመስቀሉ አጠገብ ሳለች እንኳ አላለቀሰችም እንዲያውም ረጋ ብላ እና ሰውነቷን ገዝታ በጸጥታ ሐዘኗን ተሸከመች ፡፡ ጌታ ፀጥ ያሰኛት ነገር ምን እንደሆነ አወቀ፤ የውስጧ ሐሳብና ስሜት ምን እንደሆነ ያውቅ ነበር፡፡ ስለዚህ እርሷ ሳታናግረው እርሱ አናገራት ቅድስት እናቱም ለልጇ በመታዘዝ ከሚወደው ደቀመዝሙር ጋር አብራ ለመኖር ሄደች፡፡

ድንግል ማርያም ዮሐንስ ለጌታ ስለነበረው ፍቅር ጌታ ለዮሐንስና ለቤተሰቡ የሰጠው እውነተኛ ጸጋ እውነተኛ በረከት ነበረች ቅዱስ ዮሐንስ እንደ ልዩና ድንቅ ስጦታ አድርጎ ተቀበላት ፡፡ እስከ ጊዜ ዕረፍቷም ድረስ



www.ethiopianortodox.org

www.ethiopianortodox.org

ክብካቤና አገልግሎት እያገኘች በእርሱ ቤት ኖረች ቅድስት ድንግል እስካረፈችበት ጊዜ ድረስ ቅዱስ ዮሐንስ ከኢየሩሳሌም ከተማ እንዳልወጣ ይነገራል።

ቅዱስ ዮሐንስ ጌታን እጅግ ይወደው የነበረ ከመሆኑ የተነሣ እስከ መስቀሉ ድረስ ተከተለው በሕማሙ ጊዜ ከጎኑ ነበር። በምድር ሆነ በሰማይ ለዚህ ሽልማት የሚገባው ነበር። በምድር ለሚገባው ሽልማት ቅድስት ድንግልን በቤቱ የማኖርን ታላቅ ጸጋ ተቀበለ። እንዲሁ ሁሉ ጌታን የሚከተሉ፣ የሚያምኑበትም ዋጋቸውን ይቀበላሉ፤ ጸጋውና ፍስሐውም የእመቤታችንም በረከት ይሰጣቸዋል።

ቅድስት ድንግልም በፈንታዋ ቅዱስ ዮሐንስን ልጅዋ አድርጋ ተቀበለችው ጌታም ከደቀመዛሙርት ወገን እጅግ ታማኝ አዛኝና ፍቅር ያለውን ሐዋርያ ሰጣት።

ቅዱስ ዮሐንስ ስለፍቅር እጅግ ስሜቱ ቅርብ የሆነና ስለፍቅርም ቅንአት ያለው ነበር። «እግዚአብሔር ፍቅር ነው » ሲል የተናገረው እርሱ ነው። (፩ዮሐ ፬:፩፮) በጌታ እቅፍ ገብቶ ነበር እና ጌታም እጅግ ይወደው ነበር ተብሎ የተጻፈለትም እርሱ ነው። በገጽታውም ለእመቤታችን ጌታን ይመስለው የነበረው እርሱ ብቻ ነው።

ጌታ በመስቀል ሳለ አንዳች ገንዘብ ያለው አይመስልም ነበር ። የለበሰው ልብስ እንኳ ከእርሱ ተወስዶ ዕጣ ተጣለበት ። ያኔ ለእርሱ የነበረው ደቀመዝሙሩ ቅዱስ ዮሐንስ ነበረ-ያንን ደግሞ ለእናቱ ሰጣት። ዮሐንስ ለጌታችን ልቡን ሰጠ። ጌታ ደግሞ ያንን ልብ ወስዶ ለእናቱ ሰጠ። እናቱን ያረጋጋት ከመሆኑም በላይ ወደፊት የምትኖርበትንም ሁኔታ አስተካከለላት።

እንዲሁ ሳስበው ግን ማንኛቸው ማንኛቸውን ይጠብቁ ነበር ? እያልሁ እገረማለሁ። ዮሐንስ ይጠብቃት ነበርን ወይም ቅድስት ድንግል ማርያም ዮሐንስን ትጠብቀው ነበር። ቅድስት ድንግል እኮ በዮሐንስ ቤት የነበረችው በጸጋዋና በበረከቷ ልታድሰው ልታበለጽገው እንጂ ለኑሮዋ በእርሱ ላይ ሆና እንድትተዳደር አልነበረም። በጸጋዋ የምታድሰው በመሆኗም በተጨማሪ ከጌታም ጋር ፍጹም እና ጥልቅ የሆነ ትውውቅ እንዲኖረው ልታደርገው ነበር።

ፕሮቴስታንቶች ቅድስት ድንግል ከጌታ ሌላ ልጆች ነበሯት



www.ethiopianortodox.org

ብለው የሚያሰሙትን የተሳሰተ ትምህርት ጌታ እናቱን ለቅዱስ ዮሐንስ አደራ መስጠቱ ያለጥርጥር የሚያከሽፈው ፣ የሚረታው ነው፡፡ ይህማ ቢሆን ኖሮ እርስዋን ለመጠበቅ ከዮሐንስ ይልቅ ከልጆቿ አንዳቸው በተሻሉ ነበር፡፡ ነገር ግን እመቤታችን በወቅቱም ሆነ እስከ ዕለተ ዕረፍቷ ከጌታ በቀር ሌላ ቤተሰብ አልነበራትም፡፡ ልጆችም አልነበሯትም ፤ ለጊዜው ዮሴፍም ጠባቂዋ እንጂ ሌላ ምንም አደራ አልተቀበለም ከሞተም ብዙ ጊዜ ሆኖት ነበር ፡፡ ስለዚህም ጌታ እነሆ ልጅሽ ሲል ለዮሐንስ አደራ ሰጣት፡፡ **«እነሆ ልጅሽ** » የሚለው ቃል በእናት እና በልጅ መካከል ያለውን መንፈሳዊ የሆን ግንኙነት የሚያስረዳን እና ለድንግልም የተሰጣትን ክብር ገልጾ የሚያሳየን ነው፡፡

## <u>አራተኛው ቃል</u>

«አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውኸኝ» (ማቴ፳፯:፵፮)

ይህ አነጋገር የጌታችን አምላክነቱ ሰው ከመሆኑ ተለየ ወይም አብ ልጁን ወልድን ተወው የሚል ትርጓሜ የሚያመጣ አይደለም፡፡ ይልቅስ ትርጓሜው አብ ልጅ ሕማምን ይቀበል ዘንድ ፈቀደ ማለት ነው እንጂ፡፡

አምላክነቱና ሰውነቱ ለዐይን ጥቅሻ ያህል እንኳ አልተለያየም ፡፡ የምናምነው ፣ በቅዳሴም ጊዜ የምንመሰክረው ይህንኑ ነው፡፡ ሰው በመሆኑ አምላክነቱ ተለየው የምንልማ ቢሆን የማዳን ሥራው እርሱ ሰው ከመሆኑ አስቀድሞና እርሱ ሰው ከሆነ በኋላ ለነበሩት ላሉትና ለሚኖሩት ትውልድ ሁሉ የሚሆን የሚበቃ የሚያከናውን ነው ለማለት ባልቻልን ነበር፡፡ ስለዚህ በአምላክነቱና ሰው በመሆኑ ምንም መለያየት የለም፡፡

ከአብ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ አብ አልተወውም ነበር፡፡ ይህን ቃል ብቻ እንገንዘብ፤ **«እኔ በአብ እንዳለሁ፤ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ** » (ዮሐ ፲፬:፲፩)

ታዲያ **«ለምን ተውኸኝ»** የሚለው ቃል ትርጓሜው ምንድን ነው ?

መለያየትን የሚጠቁም ቃል አይደለም፡፡ ወልድ ሕማምን እንዲቀበል ፣ ስለኃጢአትም ነቀፋንና የእግዚአብሔርን ቁጣ እንዲሸከም አብ መፍቀዱን የሚያሳይ ቃል ነው እንጂ፡፡ ይህ በስሜት ስለደረሰበት ሕማም ነው፡፡



www.ethiopianortodox.org

በአካሉ ስለተቀበለው ሕማም ደግም ምንም እንኳን በከሃሊነቱ ወልድ ሕማም የማይሰማው እንዲሆን ማድረግ የሚቻለው ቢሆንም ነገር ግን በአካሉ ሕማምን እንዲቀበል እንዲታመምም ፈቀደ፡፡ ወልድ ሕማም የማይሰማው እንዲሆን ቢያደርግ ኖሮ የስቅለቱ ነገር ዋጋ ባልኖረው ነበር፡፡ ለሕማም ቅጣት ተፈጸመ ሊባል አይችልምና ፤ ያለ ቅጣትም ምሕረት፣ ያለ ምሕረት ደግሞ መዳን አይገኝምና፡፡

ስለዚህም አብ ወልድ ሕማምን እንዲቀበል ፈቀደ፡፡ ወልድ ደግሞ ይህንኑ ፈቅዶ ሕማምን ተቀበለ፣ ታመመ፡፡ ወልድ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ምክንያትም ይኸው ነው፡፡ ወደዚህ ዓለም የመምጣቱም ነገር አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስም በአንድ አምላክነታቸው የፈቀዱት፣ የወደዱትና የወሰኑት ጉዳይ ነው፤ ስለ ሰው ልጆች በጎነትና ስለ አምላካዊ ፍርድ መፈጸም ፡፡

እግዚአብሔር አብ ልጁ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ እንዲያቀርብና እንዲታመም ፈቀደ እንጂ ወልድን አልተለየውም፡፡ ወልድም ተላከ እንጂ አልተነጠለም፡፡ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ይታመም ዘንደ አሳልፎ ሰጠ እንጂ ወልድን ፍጹም ይወደው ነበር፤ ነገር ግን « ደዌያችንን ይቀበል ዘንድ ፈቀደ ፡፡» (ኢሳ ፶፫፡፲)

እስቲ ይህን ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ ሐሳቡን ለመገንዘብ እንድንችል አንድ ምሳሌ እንውሰድ፡፡

አንድ ልጅ አካሉ በአንድ ምክንያት ቆስሎ ቁስሉ ፈሳሹ ይዞ ሲያመው ከአባቱ ጋር ያን ለመታከም ወደ ሐኪም ቤት ሄደ እንበል ፡፡ ሐኪሙም ቁስል የያዘውን ያልተፈለገ ፈሳሽ ቁስሉን በጥቶ ለማውጣት ስለፈለገ ያን እስኪያደርግ አባት የልጁን እጅ ጥርቅም አድርጎ ይይዛል፡፡ ልጁም አባቱ ሐኪሙ ቁስሉን እንዳይነካ እንዲያደርግለት «ፈልጎ አባቴ ለምን ትተወኛለህ » እያለ ይጮሃል፡፡

አባት ግን የቁስሉ መበጣት (መፍረጥ) ለልጁ የሚበጅ እንደሆነ ስለሚያውቅ ለልጁ ካለው ፍጹም የሆነ ፍቅርና ክብካቤ የተነሣ ልጁ እያመመው ዝም ማለቱ የአባትና ልጅ ዝምድናቸው ቀርቷል እንደማያሰኝ ሁሉ አስቀድመን ያነሣነው ዓውደ ንባብ ጌታ ተውኸኝ ማለቱ አብ ወልድ «ተወው» አያሰኝም፡፡ «ተውኸኝ» የሚለው ቃል የመሰቀሉ፣ የመታመሙም ነገር እንደተከናወነና ጌታ ስለኃጢአታችን መሥዋዕት ሆኖ



www.ethiopianortodox.org

ታላቅ ካሳ እንደፈጸመልን ያስረዳል። አብ ስለዚያች ሕማም ልጁን አሳልፎ የመስጠቱ ነገር በመስቀል ስለድኅነታችን ከሆነው ሕማም ሁሉ እጅግ ከፍተኛው፣ የሚበልጠውም ነው ።

ጌታ **«አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ«** ብሎ በተናገረ ጊዜ እንዲሁ በሚል ቃል የሚጀምረውን የዳዊትን ፳፩ ኛ መዝሙር ጌታ ለአይሁድ እያስታወሳቸው እንደነበረ ብዙ የትርጓሜ መምህራን ያስተምራሉ። ስለዚህም ይህ ቃል መጻሕፍት ስለእርሱ የሚመሰክሩ ሆነው ሳለ (ዮሐ ፭:፴፱) አይሁድ ግን መጻሕፍትን ባለማወቃቸው እንደሚስቱ (ማቴ ፳፪፤፳፱) የተጻፈው ነው። ጌታም መዝሙር ፳፩ የተጻፈውን ሊያስታውሳቸው «አምላኬ አምላኬ» በማለት ተናገረ። አይሁድ ግን የመዝሙርን ክፍል በመዝሙሩ የመግቢያ ሐረግ እንጂ በቁጥር ከፋፍሎ መለየት ልማድ አልነበራቸውምና።

ይህ የመዝሙር ክፍል ስለጌታ ምን ይነግረናል? በማለት ጠየቁ «. . . እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ። አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ። እነርሱም አዩኝ ፣ ተመለከቱኝም። ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ። በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ። (መዝ ፳፩:፲፮-፲፰) ማለት የተናገረውን የቅዱስ ዳዊት እጆቹንና እግሮቹን ማንም እንዳልቸነከረበት በልብሱም ዕጣ ተጣጥሎ የተከፋፈለ ምንም ሰው እንደሌለ ግልጽ ነው። ዳዊት ይህን በትንቢት የተናገረው ስለ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕማማተ መስቀል መሆኑን ልብ ይሏል። ጌታም በመልዕልተ መስቀል

**«አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ** ?» በማለት መናገሩ ቅዱስ ዳዊት ይህን የተነበየው ስለ እርሱ እንደሆነ አይሁድ እንዲረዱና በእርሱ እንዲያምኑ ነው። በተጨማሪም «የሰው ማላገጫ፣ በሕዝብም ዘንደ የተናቅሁ ነኝ የሚያዩኝ ሁሉ ይላገዱብኛል። ራሳቸውን እየነቀነቁ በክንፈሮቻቸው እንዲህ ይላሉ፤ በእግዚአብሔር ተማመነ እርሱንም ያድነው ፣ ቢወደውስ ያድነው» (መዝ ፳፪:፮-፰) የሚለው ስለ እርሱ እንደተጻፈ ሊያስገነዝባቸው በመፈለጉ የዳዊትን መዝሙር ጠቀሰላቸው።

የዚህም መዝሙር ሙሉ ክፍል እንመልከተው እንረዳው ብንል ሥፍራውም አይበቃንም። ጌታ በመስቀል የተቀበለውን መከራ ገልጾ የሚያስቀምጥ ነው። «በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አዕምሯቸውን ከፈተላቸው።» (ሉቃ ፳፬:፵፭)



www.ethiopianortodox.org

ያ የመዝሙር ክፍል የጻፈው ነገር ሁሉ እየተፈጸመ መጣ፡፡ ስለዚህም ጌታ ይህን ከተናገረ ከጥቂት ቆይታ በኋላ «ተፈጸመ» ብሎ ተናገረ፡፡ ታዲያ ለምንድነው «አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ» ብሎ ከተናገረ በኃላ «ተፈጸመ» ሳይል የቀረው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ በመዝሙር ፳፪ ከተጻፈው ነገር አንድ ገና ያልተፈጸመ ቃል መኖሩ ነው፡፡ «ኃይሌ እንደገል ደረቀ በጉሮሮዬም ምላሴ ተጠጋ » የሚለው ቃል ገና አልተፈጸመም ነበርና (መዝ ፳፪፤፲፭ ) «ተጠማሁ» ብሎ ጌታ በተናገረበት ሰዓት ይህ ቃል ተፈጸመ፡፡ ስለዚህም ጌታ «ተጠማሁ» ብሎ ከተናገረ ከጥቂት ቆይታ በኋላ «ተጠማሁ» አለ፡፡

አንድም ጌታ ስለምን «አምላኬ አምላኬ »አለ? ብንል ይህን ያለው ፍጹም ሰው መሆኑን ለማጠየቅ በሰው ቋንቋ ሲናገር ነው፡፡ የፈጠረውን ሥጋ ለብሶ (ወነሥአ አርአያ ገብር እንዲል) በመምጣቱ በሰው ቋንቋ ተናግሯል ሐዋርያው ይህን ሲያስረዳ «ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ» በማለት ከተናገረ በኋላ አያይዞም ራሱን አዋረደ ፤ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ ፡፡ (ፊሊ ፪፡፯-፱) በማለት ለአትሕቶ ርዕስ (ራሱን ዝቅ በማድረግ) መምጣቱን ገልጾአል፡፡ ከሰው ወገን እንደመወለድና የሰው ባሕርይ ያለው እንደመሆኑ የሰውን ሥፍራ ወሰደ፡፡ በእግዚአብሔርም ፊት በሰው ልጅ ተገብቶ ከራሱ፣ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ለማስታረቅ አምላኬ አምላኬ ..... በማለት ጸሎት አቀረበ፡፡

ስለዚህም **«አምላኬ አምላኬ»** በሚለው ቃል በክርስቶስ አማካይነት ሰው ልጅ ሁሉ ወደፈጣሪው ሲጣራ እናያለን፡፡ እርሱ ኃጢአታችንን ሁሉ ተሸክሟልና ፣ ኃጢአት ደግሞ ከእግዚአብሔር የሚለይና የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚያመጣ ነውና በክርስቶስ የሰው ወገን ሁሉ «አምላኬ! አምላኬ ለምን ተውኸ »እያለ ይጮሃል፡፡

አዳምና ሔዋን አትብሉ ከተባሉት ፍሬ መታቀብ ሳይችሉ ቀርተው ከዚያ ቀጥፌው በሉ፡፡ ክርስቶስ ግን ሰው እንዲበላ ከተፈቀደለት ምግብ እንኳ በመከልከል ጾመ፡፡ መጾም ከቶም የማያስፈልገው ሆኖ ሳለ ለአርባ ቀንና ለአርባ ሌሊት ጾመ፡፡

ሕገ እግዚአብሔርን በማክበርም አብነት እናደርገው ዘንድ ሕግ መጽሐፋዊ ፈጽሟል፣ ሕገ ዕብራውያንንም ተምሯል፡፤



www.ethiopianortodox.org

«የሚያስተውል ፣ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ እንዳለ ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ። ሁሉ ዐመጹ በአንድነትም ። ረከሱ።»(መዝ ፲፬:፪፫)

ክርስቶስ ጽድቅን ሁሉ በመፈጸምም ሕግጋትን ፈጸመ ይህም የሚገባ እንደሆነ ዮሐንስ ሊያጠምቀው በሆነ ጊዜ ተናግሯል።

(ማቴ ፫:፲፭) ስለዚህ ቅደመ እግዚአብሔር ንጽሕና ነቀፋ የሌለበትን ሕይወት ለመኖር ስለ ሰው ፈንታ ሆኖ እንዲህ በጽድቅ ተመላለሰ።

በሞት፣ በሕማምና ኃጢአትንም በማንጻት ስለ ሰው ፈንታ አከናውኗል፣ ወክሎናል።

«እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለእኛ ኃጢአት አደረገው።» (፪ቆሮ፭:፳፩) እግዚአብሔር በኃጥአን ላይ የነበረውን ቁጣ ከነምሬቱ እርሱ ተሸከመ። የሰዎችን ወገን የሚወክል እንደመሆኑም «አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ» ሲል ተናገረ። ሁሉን ሲረዳ የነበረና ማንንም ያልተወ እርሱ በሁሉ ዘንድ የተተወ ሆነ፣ አብም እንኳ አሳልፎ ሰጠው። በዚህ መልኩ የእግዚአብሔርን መዓት እርሱ ተሸክሞ ዕዳችንን ከፈለ፤ በሥጋው መከራን ከተቀበለ በኋላ በሞቱ ሞትን አሸነፈ፤ ሙታንን ያድን ዘንድ የማይሞተው ሞተ፣ ሞትን ይሽረው ዘንድ ሞተ። በሦስተኛውም ቀን ሞትን ድል አድርጎ ተነሣ። በዚህ እኛም ቁጥብና ጠንቃቃ ሆነን መመላለስ እንደሚገባን ዐቢይ ትምህርት ሰጥቶናል።

ኃጢአት ይህንን ሁሉ መከራና ብቸኝነት የሚያስከትል ከሆነ ዘንድ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው እንዳንመላለስ በጥንቃቄ ልንጠበቅ ይገባነናል ።(ኤፌ ፭:፲፭) እግዚአብሔር ደግሞ በፈንታው እንዳይተወን የእግዚአብሔርን መንገድ ላለመተው አስቀድመን በማስተዋል መራመድ ይገባናል። ስለኃጢአት ወልድ እንኳ የተተወ ሆኖ ነበርና። መተውና ብቸኝነት ደግሞ ስቃዩ እጅግ ከባድ ነው ። ክብሩን ትቶ እንዲህ ያለውን መከራ የተቀበለውን ጌታችንን እንዲህ ላለው ፍቅሩ ልናመሰግነው ይገባናል። ችግር በሚገጥመን ጊዜ «ለምን ተውኸኝ» የሚለው ቃል መጽናናትን የሚሠጠን ሊሆን ይገባል። እግዚአብሔር « ለገዛ ልጁ ያልራራለት »እንደሆነ (ስለኃጢአት )እያወቅን እግዚአብሔር በእኛ እንዲሆን ስለሚፈቅደው መከራ ለምን እናጉረመርማለን እኛ



www.ethiopianortodox.org

ቅጣት የሚገባን ሆነን ሳለ እኛ የጌታን ያህል እንግልት ከቶም ሊደርስብን የማይችል ሆኖ ሳለ በፈተናችን ወቅት ለምን እናማርራለን? ወልድ አብ ያቀረበለትን ጽዋ በፈቃደኝነት ጠጣ እንደፈቃድህ ይሁን ብሎ እስከመስቀል ሞት ድረስ ታዘዘ፡፡ ለምን ተውኸኝ የሚለው ቃሉ አስቀድመን እንደገለጽነው በእኛ ገብቶ (ምትክ ሆኖ) የተቀበለውን መከራ ጽኑዕነት የሚያሳይና የድኅነት ነገርም እውን መሆኑን የሚያውጅ እንጂ መከራ ለምን ጸናብኝ የሚል ቅሬታ አይደለም፡፡

## አምስተኛው ቃል "<u>ተጠማሁ</u> " (ዮሐ ፲፱:፳፱)

ስለሁላችን ኃጢዓት ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ኃይሌ እንደገል ደረቀ፣ በጉሮሮዬም ምላሴ ተጣጋ» ሲል ተናገረ፡፡ (መዝ ፻፳፪:፲፭)

የሰውነቱ ፈሳሽ ሁሉ በብዙ ነገር ምክንያት ተሟጦ አልቆ ነበር ፡፡ በአንድ በኩል ስለእኛ ድኅነት በጌቴሴማኒ የአትክልት ሥፍራ ሲደክም ብዙ ላብ ፈስሶት ነበር፡፡ ስለዚህ ነገር በሉቃስ ወንጌል ፳፪:፵፬ እንዲህ ተጽፏል፤ «ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበር፡፡ » በቀትር በምታነደው ጸሐይ ረዥም መንገድ መስቀሉን ተሸክሞ እስከ ጎልጎታ ሲጓዝም ብዙ ላብ ፈስሶታል ፡፡ በፍርድ አደባባይ ለረዥም ሰዓታት በመቆሙ፣ በአለንጋ በመገረፉ እንዲሁ ደክሟል ፡፡ በዚያም ላይ የአለንጋው ግርፋትና የእሾህ አክሊሉ ቆዳውን በስቶ በመግባቱ የፈሰሰው ደምም አለ፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ምላሱ በጉሮሮው ተጣጋ፣ የሰውነቱም ኃይል ሁሉ ተሟጠጠ፡፡ ስለዚህም«ተጠማሁ» አለ፡፡

በዚህ ቃሉም እሳቱ የቀረበውን መሥዋዕት መብላት እንደጀመረ ገለጸ፡፡ ሰማያዊ ፍትሕ እየተከናወነ ነበረና፡፡ ሰው በመሆኑ የለበሰው ሥጋ እየተቀበለው የነበረውን ሕማም አምላክነቱ ሊያቀልለው አልወደደም፡፡ እየተቀበለው የነበረው ሕማም ፍጹም የሆነ ሕመም ፣ አብ ለኃጢአት ይገባል ብሎ የወሰነውን የፍርድ ቅጣትን የሚያሟላ ሕማም፤ ለኃጢአት ካሳ ሊሆን የሚችል ፍጹም የሆነ ሕማም ነበር፡፡ ይህ ሕማም እንዲህ ያለው እንደነበረ፣ ወልድ «ተጠማሁ» ሲል ስለመከራው ገለጸ፡፡ ክብር ይግባውና ጌታ በመስቀል ሳለ «ተጠማሁ» በማለቱ አምላክ ነበር እንጂ ሰው አልነበረም እያሉ የሚያስተምሩ ሐሳውያን መምህራንም «ተጠማሁ»



www.ethiopianortodox.org

በሚለው ቃሉ ይሸነፋሉ፡፡ እርሱ ፍጹም ሰው የሆነ ባይሆን ኖሮ «ተጠማሁ» ባላለም ነበር፡፡

አንዳንዶች የማያስጠማ የሕይወት ውኃ ምንጭ እርሱ ሆኖ ሳለ እንዴት ጌታ «ተጠማሁ» አለ ብለው ሊደነቁ ይችላሉ፡፡ «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ» ሲል የተናገረ እርሱ ነውና፡፡ (ዮሐ ፯፡፴፯) ለሳምራዊቷም ሴት እንዲህ ብሏት ነበር፤ «እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ» (ዮሐ ፬፡፲፬) ታዲያ ጌታ በመስቀል «ተጠማሁ» ብሎ ሲናገር ምን ማለቱ ነበር ? በእርግጥም በአካሉ ተጠምቶ ነበር፡፡ ዳግመኛም በመንፈሳዊ ጎኑ ደግሞ ለዓለም የሚሰጠውን ድኅነት ለማጣጣም ተጠምቶ ነበር ፡፡

በመስቀል «ተጠማሁ» ሲል በተናገረው ቃል እና ለሳምራዊቷ ሴት «ውኃ አጠጪኝ » ሲል በተናገረው ቃል መካከል አንዳች ተመሳሳይነት አለ፡፡ ሳምራዊቷን ሴት የሚጠጣ ውኃ ሲጠይቃት እኛ የምናውቀው የ«ውኃ» ትርጓሜ አልነበረምና፡፡ የጉድጓዱ ውኃማ ቢጠጡት ዳግመኛ የሚያስጠማ እንደነበረ እራሱ ያውቃል፡፡ (ዮሐ ፬፡፯-፲፫) እርሱ የተጠማውስ የእርሷንና የሌሎች ሳምራውያንንም ሁሉ ድኅነት የምሥራቹን ሰምተው ወደ ቃልኪዳኑ መምጣታቸውን እና መዳናቸውን ነበር ፡፡

በመስቀልም **«ተጠማሁ»** ማለቱ በዙሪያው ካሉት ሰዎች የሚጠጣ ውኃ ሊያገኝ ፈልጎ አይደለም፡፡ የሚጠጣውን ሐሞት እንደሚያቀርቡለት ያውቅ ነበር፡፡ (ማቴ ፳፯፡ ፵፬-፵፰)፡፡ የወደፊቱን ለማየት የሚያስችለው አምላካዊ ኃይሉ ይህን እንዲያውቅ ያደርገው ነበርና፡፡ በመዝሙር ፷፰፡፳፱ ላይ «ለጥማቴም ሆምጣጤ አጠጡኝ »ተብሎ ስለተጻፈው ትንቢት ምክንያትም ይህ እንደሚሆን ያውቅ ነበር፡፡

የቀረበለትን የመከራ ጽዋ እስከ ፍጻሜው ሊጠጣው ፤ሊቀበለው ይወድ ነበርና «ተጠማሁ» ሲል ውኃ አምጡልኝ ማለቱ አልነበረም፡፡ እርሱ ቢያደርግ እንጂ የሰውን ልጅ አድርጉልኝ ብሎ እርዳታ የማይጠይቅ አምላክ ስለሆነም «ተጠማሁ» ሲል ከሰዎች ውኃ ፈልጎ አልነበረም፡፡ ለዚህም ነው ሕመሙን ለማስታገስ እንዲረዳው ሐሞትና ሆምጣጤ ደባልቀው ቢያቀርቡለትም ሊጠጣ ያልፈለገው፡፡ «በሐሞት የተደባለቀ



www.ethiopianortodox.org

የወይን ጠጅ ሊጠጣ አቀረቡለት ቀምሶም ሊጠጣው አልወደደም። » (ማቴ ፳፯:፴፬) ለሰዎች ድኅነት እርሱ ስለሚቀበለው መከራ የተነገሩት ትንቢቶች ሁሉ ፍጻሜን እንዲያገኙ እርሱ ወደደ። ይህ ከሆነም በኋላ ድኅነት ተከናወነች፤ የሰው ልጅ ከእንግዲህ አፎይ ለማለት ይችላል ሲል ሁሉ መፈጸሙን አሳወቀ ፡፡

ሆኖም ግን ስለእነርሱ ድኅነት ጌታ ሲደክም ክፉዎች ስለውኃ ፈንታ መከራውን ለማብዛት ሆምጣጤን እያቀረቡ ዘበቱበት። ተገዳደሩበትም። ወንድሜ ፤ እኛም አሁን እንዲሁ እያረግን ይሆንን እያልሁ አስባለሁ ። እኛ እንድንድንና በውስጣችን ሕይወት የሚሆነንን የእርሱን ቅዱስ ሥጋ እና ክቡር ደም ለመቀበል እንድንችል ጌታ ተጠማ። እኛ ግን በዚህ ፈንታ የበደላችንንና የቸልተኝነታችንን ሆምጣጤ እናቀርብለታለን ።

ወንድሜ፤ እባክህ በጌታ ላይ የደገንኸውን ጦርና ወደ ከንፈሩም ያስጠጋህለትን መፃፃ ዘወር አድርግ፣ ተወውም ። እንዲህ የወደደህን እርሱን ለማሳዘንህ ፀፀት ይሰማህ። በንስሐም ማድረግ ያለብህን ያንን አድርግ። ጌታ «**ተጠማሁ**» ብሎ ሲናገር የምትሰማው ቢሆንም እንዲህ ብለህ ምላሽ ስጠው ፤ በኃጢአቴና በበደሌ ምክንያት ምላስህ በጉሮሮህ እንዲጠጋ ያደረግኹ እኔ ነኝ ። በዕንባዬ ጥምህን ብቆርጥልህ ደስ ባለኝ። እምቢተኛ ነፍሴን ጎሽመሃት ከዚህ ከሚፈሰው ውኃ ብትጠጣም በወደድሁ!

## ስድስተኛው ቃል <u>«**ተፈጸመ**»</u> (ዮሐ ፲፱:፴)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅ እና በሁሉ ፍጹም የሆነው እርሱ ፤ ቅዱስ የሆነና አንዳችም ኃጢዓት ያልሠራ እርሱ፤ በምድር አብን ደስ ባሰኘ ፍጹም በንጽሕናና በበጎነት የተመላለሰ እርሱ፤ በማስተማርና በአገልግሎት ተግባሩም እንዲሁ ፍጹም ነበር። አብ ወልድ እንዲፈጽመው ያበጀውን ዕቅድ በሙሉ አከናውኖ ነበርና በድል አድራጊነት «ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ» ብሎ ለመናገር ቻለ። (ዮሐ ፲፯:፬)

ሕግ የሚያዝዘውን /የሚጠይቀውን የጽድቅ ተግባር በሙሉ ፈጽሞ ነበር። «ከእናንተ ስለኃጢአት የሚወቅሰኝ ማነው? » ብሎ ሲናገርም



www.ethiopianortodox.org

በእውነነት ይህን ለመናገረ የተገባው ነበር።(ዮሐ ፰:፵፮) ስለመምጣቱና ለሰው ልጆች ቤዛ በመሆን ስለሚፈጽመው የማዳን ተግባር የተነገሩ ትንቢቶችን ሁሉ ፈጸመ። ይህንንም ሠላሣ ዘመን ከመላው በኋላ በሦስት ዓመታትና ጥቂት ወራት ጊዜ ውስጥ አከናወነ። ከእርሱ በፊትም ሆነ ከእርሱ በኋላ ማንም ሰው ያላከናወነውንና የማያከናውነውን እርሱ አደረገ። ወንጌልን ሰበከ፤ ለአብም እንዲህ ሲል ለመናገር ቻለ፤ «.... በምድር አከበርኹህ ... ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው ... የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና ... በዓለም ሳለሁ የሰጠኸኝን በስምህ እኔ እጠብቃቸው ነበር ጠበቅኋቸውም - ከእነርሱ ማንም አልጠፋም።» (ዮሐ ፲፯: ፬-፲፫)

ስለዚህ ስለ እርሱ የተነገሩ ትንቢቶችን ፈጸመ፣ ጽድቅንም ሁሉ አደረገ አገልግሎትንም ፈጸመ የወደዳቸውንም እነርሱን እስከ መጨረሻው ድረስ ወደዳቸው (ዮሐ ፲፫:፩) ከዚያም የመሥዋዕትነት ተግባሩን ለመወጣት፣ድኅነትን፣ ቤዛንና ምሕረትን ለማስገኘት ፣ በሰማይና በምድር፣ በመንፈሳውያንና በምድራውያን መካከል የተጀመረውን ዕርቅ ለመፈጸም ወደ መስቀል ወጣ።

ከአዳም እስከ ዘለዓለም ያለውን ትውልድ ሁሉ ኃጢአት ተሸክሞ በመሰዊያው ላይ ቀረበ። እርሱ የተሸከማቸው የኃጢአት ምግባሮቻችንም እጅግ ክፉ ናቸው ግፈኝነት፣ ከህዲነት ስንኩልነት/ዝቅጠት፣ዝሙት ፣ ጥራዝ ነጠቅነት፣ ስርቆት፣ ነፍስ ማጥፋት፣ ቅንዓት፣ ጠበኝነት ...። ይህን ሁሉ ክፋትና የተከተለውንም መዓት እርሱ ተሸከመ። ከዚህ በኋላም «**ተፈጸመ**» ሲል ሁሉ መከናወኑንም አወጀ። እኛ ደግሞ በየዕለቱ ለምንሠራው አዳዲስ በደል የእርሱ ደም መንጻት ይሆነን ዘንድ ፣ ይቅር ይለንም ዘንድ፣ ይህን ንጹሕ መሥዋዕት እንዳስሳለን።

በኢሳይያስ ፶:፮ ላይ « ጀርባዬን ለገራፊዎች፣ ጉንጩንም ለጠጉር ነጪዎች ሰጠሁ፤ ፊቴንም ከውርደትና ከትፋት አልመለስሁም» ተብሎ እንደተነገረ፤ በመዝሙር ፳፩: ፮-፯ ላይ ደግሞ «የሰው ማላገጫ በሕዝብም ዘንድ የተናቅሁ ነኝ የሚያዩኝ ሁሉ ይላገዱብኛል» ተብሎ እንደተጻፈ ሐፍረታችን እና መዋረዳችን ሁሉ በእርሱ ላይ ሆነ ፤ ከእርሱ በፊት የነበሩ የሠሩት ግፍ ብቻም አይደለም ፤ ከእርሱም በኋላ ባለነው አስከፍጻሜው የምንሠራት ኃጢአት ሁሉ በእርሱ ላይ ተከማቸ እንጂ።



www.ethiopianortodox.org

በዚህም ምክንያት ለግርፋት፣ ለውርደትና መዘባበቻ ለመሆን ተዳረገ፡፡ በዚያን ጊዜ በፊቱ ተፉበት፣ ጎሰሙትም ሌሎችም በጥፊ መትተው፡- (ክብር ይግባውና) ክርስቶስ ሆይ በጥፊ የመታህ ማን ነው ? ትንቢት ተናገርልን አሉት፡፡ (ማቴ ፳፯ : ፴፯-፴፰) ቀይ ግምጃ አለበሱት ፣ የእሾህ አክሊልንም አቀዳጅተው «በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው » ተብሎ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ በሁለት ወንበዴዎች መካከል ሰቀሉት፡፡ (ገላ ፫:፲፫ ፣ ዘዳግም ፳፩:፳፫)

በመስቀል ሳለም ትንቢት ሁሉ መፈጸሙን አውቆ «ተፈጸመ» ይል ዘንድ ውርደትና መዘባበቻ መሆን በእርሱ ላይ ደረሰ፡፡

እንዲቀበለው የሆነው ውርደት ሁሉ ሊፈጸም በአካሉ የደረሰው ሥቃይና የእግዚአብሔር ቁጣ ሙሉ ለሙሉ ተከወነ፡፡ ጌታ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦ ዕዳችንን ሁሉ ከፈለ፤ እሳቱም የቀረበው መሥዋዕት ወደ ዐመድነት እስኪቀየር ድረስ እየተቀጣጠለ መሥዋዕቱን በላው፡፡ ( ሌዋ ፮:፲) ጌታችንም የማዳንን እና ቤዛ የመሆንን ተግባር እንደ ፈጸመ፣ ሰማያዊ ፍትሕ የሚጠይቀውን ዋጋ አሟልቶ እንደሰጠ እና የተጓደለ ነገር እንደሌለ ባየ ጊዜ **«ተፈጸመ»** ሲል ድሉን አወጀ፡፡

ለሁሉ የምትሆን ድኅነት እና ነጻነት ተከናወነች ተሳካች የሰው ልጅ የእባብን ራስ ቀጠቀጠ ፡፡ « በአሕዛብ መካከል እግዚአብሔር ነገሠ» (መዝ ፺፭-፲) ተብሎ እንደተጻፈ እግዚአብሔር በመስቀል ላይ በመንገሥ የሰይጣንን የግዛት ዘመን እና የግዛት ሥፍራ ለመደምሰስ ቻለ፡፡ የተገኘው መንጻትና ደኅነትም ሁሉን አቀፍ፤ ሁሉን ነፃ የሚያወጣ ሆነ፡፡ አሁን የቤተመቅደስ መጋረጃ ለሁለት ተከፍሏልና ወደ ውስጥ የሚወስደው መንገድ ክፍት ሆኗል፡፡

ወደ ተቀደሰው ሥፍራ ለመድረስ ይቻላል፡፡ ዕርቅ ተፈጽሟልና በዕረፍተ ነፍስ ያሉ ቅዱሳን ተስፋ ያደርጉት የነበረው ነገር ተከናውኗል፡፡ ከእንግዲህስ በኃያልነትህ ሰይፍህን በወገብህ ታጠቅ እንጂ የቀረህ ነገር የለም ሲል መዝ ፷፱: ፫ ጌታ ደስ ተሰኝቶ **«ተፈጸመ»** በማለት አሰምቶ ተናገረ ፡፡

**«ተፈጸመ»** የሚለው ቃል የደስታና የድል አድራጊነት ቃል ነው፡፡ ተዋግቶ አሸንፎአል አስቀድሞ የዚህ ዓለም ገዢ ተሰኝቶ የነበረውን የሰይጣንን አገዛዝ ለማፈራረስና የእርሱን ሰማያዊና መንፈሳዊ መንግሥት



www.ethiopianortodox.org

ለመመሥረት እንዲችል የእኛን የሁላችንን ዕዳችንን ከፈለልን፡፡

ወንድሜ፤ ጌታ ያሸነፈውን ያንን አንተ ልታሸንፍ ትችላለህን ? ወደመስቀል ወጥተህ የእባብን አናት ልትቀጠቅጥ ይቻልሃልን ?

እግዚአብሔር አቅዶ ያኖረልህን ተግባር አይተህ «ተፈጸመ» ለማለት ትችል ይሆንን? ሁልጊዜ በፊትህ ይህንን የመጨረሻውን ታላቅ ግብ ዓላማ አድርገህ ወደዚህ ብትሮጥ ምንኛ ደስ ባለኝ ? « በዚህ ዓለም እንዳደርገው የሰጠኸኝን ተግባር ፈጽሜአለሁ ...» ብለህ መናገር መቻልን ጌታ በዚህ ዓለም ሳለ በአብ በራሱ እና በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የተወጠነለትን ሁሉ ፈጽሞ የማከናወኑን ነገር ዘውትር በፊትህ አኑረው ፡፡

## ሰባተኛው ቃል

## «አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ ፡፡ »

**(ሉቃስ ፳፫፡-፵፮)**

ጌታ ለሕማም ተላልፎ እንዲሰጥ ከመሆኑ አስቀድሞ ሊያደርገው ይገባው የነበረውን የጽድቅ ተግባር ፈጽሞ እንዳከናወነ ሁሉ በመስቀል ላይ እና ከዚያ ወዲያም የነበረውን ተግባር እንዲሁ በሚገባ አሟልቶ ነው ያከናወነው፡፡

በመስቀል እንዲሞት ከሆነ በኋላ የቀረው አንድ ተግባር ነበር፡፡ ምርኮን ማርኮ ለሰዎች ስጦታን መስጠት፡፡ (ሶፎ ፬፡-፰) ወደ ሲዖል ወርዶ የምሥራቹን ለሙታን ማድረስ፤ ከአዳም ኃጢአት በኋላ ተዘግታ የነበረችውን የገነትን ደጅ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመክፈትም በዕረፍት ያሉ ቅዱሳንን ከሲዖል ወደ ገነት የመውሰድ ተግባር ይቀረው ነበር፡፡

የድኅነት ሥራ ተፈጽሞ ነበርና ይህን ከመሆን የሚያዘገየው ምንም ምክንያት አልነበረም፡፡ ለሞቱት ድኅነትን ያስገኝላቸው ዘንድ ከሥጋዊ አካሉ ሊለይ ግድ ነበር፡፡ ከሞት በኋላ እንዲያደርገው የታቀደለትን ተግባር ለማከናወን ነፍሱን ለአብ መስጠት ነበረበት፡፡ ስለዚህም «አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ» ሲል አሰምቶ ተናገረ፡፡

ነፍሴን አደራ እሰጣለሁ ለሌላ አይደለም ለአንተ እንጂ፡፡ የዚህ ዓለም



www.ethiopianortodox.org

ገዥ ይመጣል፡፡ በእኔ ላይ ግን አንዳች የለውምና (ዮሐ ፲፬ ፡ ፴)

ከአብ ወጥቼ ወደዓለም እንደመጣሁ ደግሞ ዓለምን ትቼ ወደአብ እሄዳለሁና (ዮሐ ፲፮፡፳፰) በሲያል ለራሱ እንዳስገዛቸዉ ነፍሳት የጌታንም ነፍስ ሊገዛ የዚሁ ዓለም ገዢ መከጀሉ እንደምን ያለ ድፍረት ነዉ! ነገር ግን የጌታን ነፍስ አብ ተቀበላት እንጂ የዚሁ ዓለም ገዢስ ለመቅረብ አልተቻለዉም፡፡ አሳልፎ ሊሰጣት፤ ከዚያም ከሞት ሊያስነሣት ያች የእግዚአብሔር ገንዘብ ነበረችና፡፡

ነዳዩ (ችግረኛው) አልአዛር በሞተ ጊዜ ነፍሱን መላእክት ተረከቧት (ሉቃ ፲፮፤፳፪) የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ነፍስ ደግሞ ወደ ክርስቶስ እቅፍ ገባች፤ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ነፍስ ግን አብ ተቀበላት፡፡

ማቴ ፳፯፡፶ ላይ ሐዋርያው ጌታ «በታላቅ ድምጽ ጮሆ ነፍሱን ተወ» ሲል ጽፏል፡፡ ከዚህ ቃል ምን ለመገንዘብ እንችላለን? መቼም መስቀል ተሸክሞ እንዲወድቅ እስኪሆን ድረስ በመስቀሉ ክብደትና በጉዞዉ የተነሳ ጌታ እጅግ ደክሞት እንደነበር ግልጽ ነዉ፡፡ በዚያም ላይ ከግርፋቱ፤ በችንካር ከመቸንከሩና በእሾህ ከመወጋቱ በወጣዉ ደምና ላብ የተነሣ የሰዉነቱ ፈሳሽ ተሟጦና ዝሎ 'ተጠማሁ' ብሎ እስኪናገር ድረስ ደክሞ ነበር፡፡

ታድያ እንዲሁ ደክሞ ሳለ እንደምን በታላቅ ድምጽ ሊጮህ ቻለ? ለሞት በተቃረበበት ሰዓት በታላቅ ድምጽ ጮኾ ማለት ከሰብዐዊነቱ አልፎ የሚሄድ አንዳች ኃይል በዉስጡ እንዳለ የሚያሳይ ነዉ፡፡ ጌታ በሞት ሞትን አሸንፎአልና በታላቅ ድምጽ መጮሁ ይህን ድል አድራጊነቱን የሚጠቁም ነዉ፡፡ ይህ ታላቅ ድምጽ ሰይጣንን አነዋዉጾ መንግሥቱን ሽሮታል በእዉነት የጌታ ሞት እባብን የረገጠበትን መላዉን ዓለም ያዳነበት ድል ነበር!

**«ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ»** የሚለዉ ቃል ነፍስ የማትሞት የማትበሰብስ ስለመሆኗ በእርግጠኝነት እንድናዉቅ የሚያስተምረን ነዉ፡፡ ሞት ለነፍስ ፍጻሜዋ አይደለም– ከአንድ ዓይነት አኗኗር ወደሌላ ዓይነት አኗኗር መሸጋገሪያዋ ብቻ እንጂ፡፡ ጥያቄዉ ነፍስ ከሞት በኋላ ወዴት ትደርሳለች፤ መግቢያዋ የት ነዉ የሚለዉ ነዉ፡፡ ሰዉ ለዚህ ጥያቄ መልሱን በእርግጠኝነት ካወቀው እንደ ቅዱስ ጳዉሎስ 'ልሔድ



www.ethiopianortodox.org

እናፍቃለሁ’ ብሎ ሞትን በደስታ ይቀበላል። ወንድሜ ከሞት በኋላ ነፍስህ ወደየት እንደምትሔድ ተማምነሃልን? እርግጠኛ ነህን? ከረዥም የሕይወት ጊዜ ቆይታ በኋላ ነፍስህን ስታስረክብ ለክርስቶስ ወይም በአልኣዛር ጊዜ እንደሆነዉ መላእክት ተረክበዉ ወደላይ እንዲያደርሷት ነውን? ወይስ «ይህች ነፍስ የእኔ ናት፣ በሥሬ ከነበሩት ወታደሮቼ አንዷ ናትና ከእኔ ዘንድ እንድትሆን እወስዳታለሁ .......»እያለ በመናገር ሊረከባት የሚመጣው ሰይጣን ነው? አቤት ይህ እንዴት የሚያሰቅቅ ሐሳብ ነው! እንግዲያውስ ወንድሜ.... የነፍስህ መሄጃዋ በእርግጥ የታወቀ እንዲሆንልህ ይህን ብታስተማምን አይሻልም ትላለህን ?

የተወደድህ ወንድሜ ዘወትር ይህን መልካም ዝማሬ ከፊትህ አኑረው.... አትዘንጋውም «የጻድቃንን ሞት እኔ ልሙት፤ ፍጻሜዬም እንደ እርሱ ፍጻሜ ትሁን» (ዘኁልቁ ፳፫:፲) ክፉን ነገር ሁሉ በማራቅና አካሄድህን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረግ ከአሁን ጀምሮ ነፍስህን ለእግዚአብሔር አደራ ሰጥ። እግዚአብሔር በቀኝ እጁ ይዞአቸው እንደነበሩት እንደ ሰባቱ ቤተክርስትያን መላዕክት (ጠባቂዎች) ሁን። ራስህን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እጅ መሀል አኑር።«የዘለዓለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ ለዘለዓለም አይጠፉም፣ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም ... ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም » የሚለውን ደስ የሚያሰኝ ከሚሰሙት ወገን መሆንህን ታስረግጥ ዘንድ ያ እንደሚገባህ ሆነህ ኑር። (ዮሐ ፲:፳፰-፳፱) ኃጢአትና የሥጋ ምኞት በተፈታተኑህ ጊዜ እንዲህ ስትል ራስህን ጠይቅ፤ «አሁን በዚህች ሰዓት ነፍሴ በጌታ እጅ በጌታ ዘንድ ናትን?»

## ማጠቃለያ።

## <u>ጌታ በመስቀል የተናገራቸው ቃላት</u>

## <u>ከሕይወታችን አንጻር ምን ያስተምሩናል?</u>

ጌታ በመስቀል የተናገራቸው እኒህ ሰባቱ ቃላት ለሁላችን ገንዘብ ተደረገው ሊታሰቡ ፣ ሊታዩ ሊመረመሩ የሚገባቸው ናቸው ። ሕይወታችንን እንዲያበጁት፣ ለሕሊናችን ዘልቀው የሚሰሙ እንዲሆኑ፣ ለእያንዳንዷ ቃላትም ኑሯችንና አካሄዳችን አንጻራዊ ምላሽ የሚያሳይ እንዲሆን ልናደርግ ይገባናል ። ይህን እንዴት ለማድረግ እንደምንችል



www.ethiopianortodox.org

እስቲ ሁለት ምሳሌዎችን እንመልከት ፡፡

**➔ አባት ሆይ ይቅር በላቸው፡፡**

ጌታችን ጸሎትን ሲያስተማረን «እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን »በማለት እንድንጸልይ ነው፡፡ ስለዚህ አንተ ምሕረትን እንድታገኝ አስቀድመህ «አባት ሆይ ይቅር በላቸው » በማለትህ ቅድሚያ የሚፈለግብህ ዋጋ እና ማሟላት የሚገባህ ግዴታ ነው ማለት ነው፡፡

ማንም ሰው ቢሆን ግን ስለሌሎች «አባት ሆይ ይቅር በላቸው » ብሎ በመጸለዩ ለእኛ ሰዎች ምሕረትን፤ ይቅርታን የሰጠ፤ ያደረገ አይምሰለዉ፡፡ ይህን በመናገሩስ ምህረትን የሚያገኘዉ ራሱ ነዉ እንጂ፡፡ ሌሎችን ይቅር ማለት ለራስ ምሕረት የማግኛ በር ፤ ለራስ ምህረት የመግዣ ገንዘብ ነዉና፡፡ 'ይቅር በሉ ይቅርም ትባላላችሁ' ተብሎ እንደተጻፈ (ሉቃ ፮፤፴፯)

ጌታ አቡነ ዘበስማያት የምንለዉን ጸሎት ካስተማረ በኃላ በጸሎት ካሉት ቃላት ሁሉ ተጨማሪ ትምህርትን አስከትሎ የሰጠበት ቃል ስለ ይቅርታ የሚናገረዉን ክፍል ነዉ፡፡ እንዲህ ይላል፤ «ለሰዎች ኃጢአታቸዉን ይቅር ብትሉ ሰማይ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኃልና፡፡»

ማቴ ፮፤፲፬፣፲፭ ስለዚህ ሌሎችን ይቅር የማትል ከሆነ ደግሞ ሌሎችን ሳይሆን ራስህን ከይቅርታ ዉጪ ታደርጋለህ ማለት ነዉ፡፡ «አባት ሆይ ይቅር በላቸዉ» ብለህ ብትለምን ግን እርሱ ደግሞ «አንተንም ይቅር እልሃለሁ» ሲል ይመልስልሃል፡፡ ስለዚህ አንተ ይቅርታን እንድታገኝ የምትሻ ብትሆን ሌሎችን ይቅር ማለትህ ግድ ይሆናል፡፡ የበደሉህን ይቅር ማለትህ ለራስህ ምህረትን ለማግኘት አስቀድመህ መፈጸም ያለብህ ግዳጅ ስለሆነ ብቻ ነዉ ለአንተ የሚበጅህ፡፡

ምናልባት እንዲህ ያለዉ ምሕረት ማድረግ (ይቅር ማለት) ሕሊናህ ባስቀመጠዉ ምክንያታዊ መስፈርት ሲለካ 'ተገቢ ነዉ' ብለህ የምታምንበት ዓይነት ስለማይሆን ዉስጥህን ሊያበሳጨዉ ሊያናድድህም ይችላል፡፡ እንደዚያ ከፍ ዝቅ አድርጎ ያዋረደኝንና ያበሳጨኝን እንዴት



www.ethiopianortodox.org

ይቅር ልለዉ እችላለሁ? የሚል ሃሣብ ሊያብከነክንህ ይችላል፡፡ እኔ ግን ይህን እነግርሃለዉ፤ እንዲህ የሚታገልህን ስሜት ዝም ብለህ ቻለዉ- ታገስም፡፡ ይህን ሰዉ ይቅር ስትል ራስህንም ይቅር እያሰኘህ ነዉና እግዚአብሔር ይቅር እንዲልህ ይቅር በል፡፡ ደግሜ የምነግርህ ነገር ደግሞ ይቅርታህ ከግዳጅ ሳይሆን ከፍቅር የመነጨ እንዲሆን ነዉ፡፡

ጌታ ለሕዝቡ ሁሉ ይቅርታን ሊያስገኝ ወደመስቀል በወጣ ግዜ ተግባሩን የጀመረዉ አስቀድሞ የሚሰቃዩትን ይቅር በማለት ነበር፡፡ አካሄዱ ልክ 'እኔን ይቅር ትለኝ ዘንድ እኒህ በእኔ ያደረጉብኝን ሁሉ ይቅር በላቸዉ' እያለ እንደመናገር ነበር፡፡ ይህን ማድረጉ አብ እርሱን ይቅር እንዲለዉ አይደለም፤ በዮሐ ፰፡፵፮ እርሱ ራሱ 'ከእናንተ ስለኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነዉ?' ብሎ እንደተናገረ እርሱ አንድም ኃጢአት አንድም ነዉር አልነበረነትምና፡፡ 'የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ' ነበርና (ዮሐ ፩፡፳፱) እግዚአብሔርም የሁላችንንም በደል በእርሱ የተሸከመዉን ኃጢአት ይቅር ያስብል ዘንድ ፤ ያን ኃጢአት ያስሠርዝ ዘንድ ምህረት አድርጎ ምህረትን ጠየቀ፡፡

አንተ ግን 'የበደሉኝን መታገሴ፤ ክፋታቸዉን በክፋት አለመመለሴ አንሶኝ እንዴት የበደሉኝን ሁሉ 'ይቅር' እላቸዋለሁ? መታገሴ አይበቃኝምን?' ብለህ ትጠይቅ ይሆናል፡፡

አይደለም ልጄ! ክፉን በክፉ ሳትመልስ መታገስህን ብቻዉን አይበቃም፡፡ በዉስጥ የሚፈታተንህን ስሜት አሸንፈህ በፈቃደኝነትና በፍቅር ይቅር ማለት አለብህ፡፡

መስቀል ላይ ስትወጣ ደግሞ «እርሱንና የትንሣኤዉን ኃይል እንዳዉቅ፤ በመከራዉም እንድካፈል» ብለህ ለመናገር ያኔ ትችላለህ፡፡ (ፊሊ ፫፡፲) በመከራዉ ተካፍለህልና፤ እርሱን መስለህ ወደመስቀል በመዉጣት የሚያደርጉትን ለማያዉቁ እና የበደሉሁን ሰዎች ይቅር ብለሃልና፤

### ➔ «ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ»

'ይህንን ቃልኪዳን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ልቀበል ከወደድሁ አእንደፈያታዊ ዘየማን 'ስላደረግነዉም የሚገባንን እንቀበላለንና' ነዉሬን አምኜ የሚደርስብኝን ሁሉ ልቀበል ይገባኛል' እያልህ ለገዛ ራስህ ንገረዉ፡፡



www.ethiopianortodox.org

ፊያታዊ ዘየማን በፍርድ የደረሰበትን ስቅላትና የተቀበለዉን ሕማም 'ለምን' ብሎ አልተማረረም አልተከራከረም። እርስ የፈለገዉ በዘለዓለማዊ ሕይወቱ ይቅር መባልን፤ ምህረት ማግኘትን ብቻ ነበር። ይህን ምሳሌ ልንከተል እንጂ ከመስቀል ወርደህ እኔንም እንድወርድ አድርገኝ ብሎ ጌታን እንደተገዳደረዉ እንደ ፊያታዊ ዘፀጋም ልንመስል አይገባንም።

በግራ የተሰቀለዉ ወንበዴ ልቡ ጠማማ ነበርና ራስህንም እኛንም አድን እያለ ይናገር ነበር። ጌታ ከመስቀል ቢወርድማ ዓለም ከእነርግማኗ በኖረች ነበር። በግራ የተሰቀለዉ ወንበዴ ይህንን የሚያዉቅ ቢሆን ኖሮ በቅንነትም የነፍሱን ድኅነት የሚሻ ቢሆን ኖሮ እንዲሁ እያለ በተናገረ ነበር--"ጌታ ሆይ ስለ እኔ፤ እኔ እንዳልጠፋ ስትል እባክህን ትንሽ በመስቀልህ ላይ ቆይ። ስለ እኔ ሕማምህን ታገስ ጌታ ሆይ፤ ስለኃጢአቴ ሁሉ የሚገባዉን ዋጋ ትከፍል ዘንድ እስከሞት ታገስ . . "።

ወንድሜ፤ ለዘለዓለማዊ ሕይወቱ ጉዳይ ይጨነቅ እንደነበረዉ እንደ ፊያታዊ ዘየማን መንፈሳዊ ሁን እንጂ ሥጋዊ አትሁን።

በተጨማሪም በሕይወትህ በሚገጥምህ መከራ ሁሉ በቀኝ እንደተሰቀለዉ ወንበዴ 'ስላደረግነዉም የሚገባንን እንቀበላለንና' በል እንጂ ለምን ሆነ ብለህ አታማረር አታፈግፍግ።

'በመንግሥትህ አስበኝ' ብለህ ጌታን ከጠየቅህ ዘንድ አንተ ደግሞ በፈንታህ በምድር ሳለህ እርሱን ማሰብ፣ በፍቅርና በአምልኮም እርሱን ሙጥኝ ማለት ይገባሃል።

እግዚአብሔር በሰማያዊ መንግሥቱም እንዲያስብህ ጭምር ጠይቀው እንጂ ስለምድራዊ ሕይወትህ ብቻ መጎብኘትን ምትለምነው አትሁን። ይህች ምድር ለአንተ ያዘጋጀችልህ ችንካሮች፣ መስቀሎች፣ መከራዎች . . .ምንም ይሁን ዋናው መታሰብ ያለበት ነገር በሰማያዊው መንግሥት የሚኖርህ የወደፊቱ ሕይወትህ ነው ።

ቁምነገሩ በገነት ከጌታ ጋር መሆናችን ነው እንጂ ምድራዊ ሕይወታችን በመስቀል እንደተቸነከርን ብናሳልፈውም የሚጎዳን ነገር የለም፣ አያሳስብምም።



www.ethiopianortodox.org

ታገስ እንጂ ከመስቀልህ ለመውረድ ቀዳዳ አትፈለግ፡፡ ጌታ በቀኝ የተሰቀለውን ወንበዴ እምነቱን ፣ ንስሐውን እና ስለኃጢአቱ ማዘኑ የተፀፀተውን ፀፀት ስለተቀበለው «ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ» አለው፡፡

አንተስ .... በገነት ከእርሱ ጋ ለመሆን የተገባህ ትሆን ዘንድ እምነት፣ ንስሐን እና ስለኃጢአት ማዘንን ለእግዚአብሔር አቅርበህለታልን? እስከ አሁን ይህን ያለደረግህ ቢሆን በል አሁን ተነሥና ተግባርህን ጀምር! ከእርሱ ጋር አበረኸው ትከብር ዘንድ እንዲሁ ደግሞ በመከራም እርሱን ለመምስል...መከራን ተቀበል፡፡

«ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ» የሚለው ቃል እጅግ የሚያፅናና፣ በሐሴትና በተስፋ የሚሞላ የሚያለመልምህ እንደሆነ አስታውስ፡፡

ወንበዴው በገነት ትሆናለህ የሚል ቃለ ኪዳንን የተቀበለ ከሆነ አንተ ደግሞ የሠራኸው ኃጢአት ምንም ይሁን ምን ተስፋ ልትቆርጥ፣አይሆንልኝም ብለህ ልትሳነፍ አይገባህም፡፡ ወንበዴው በሕይወቱ ማብቂያ የመጨረሻዋ ደቂቃ ያቀረበው ንስሐ ተቀባይነት ካገኘ፤ አንተም የቀደመ ሕይወትህ በሙሉ በብኩንነት ያለፈ ቢሆንም እንኳ ተስፋ መቁረጥ የለብህም፡፡

ጌታ ለወንበዴው ያደረገው የቸርነት ሥራ ለጸሎታችን የእግዚአብሔር ምላሽ ምን ያህል ፈጣን ሊሆን እንደሚችል በሚገባ የሚያሳይ ነው፡፡

ወንበዴው ገና «ጌታ ሆይ በመንግሥትህ አስበኝ » ከማለቱ ወዲያው «ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ » የሚል ምላሽ አገኝ፡፡ ስለዚህ በጸሎትና በልመና ትጋ «ጌታ ሆይ አስበኝ » ማለትም አትዘንጋ ፡፡ በእምነት እና ከልብ በሆነ ስሜት ሆነህ ደግመህ ደጋግመህ ይህንን ጸልይ፤ እግዚአብሔር ምላሽ እንደሚሰጥህም እርግጠኛ ሁን፡፡

ለሰይጣን እጅ ሰጥተህ ተከትለህ በሚመጡብህ ሀፍረት ወይም ትዕቢት ምክንያት « አስበኝ » ብለህ ከመለመን መከልከልን በራስህ ላይ አታምጣ፡፡ እንዳይገጥምህም አስቀድመህ አንተም ለሰይጣን እጅህን አትስጥ፡፡ ቁራጭ ስለኃጢአት በታላቅ ሀፍረት ሆኖ « ጌታ ሆይ ይቅር በለኝ » ሲለ በቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ ደግሞ የኃጢአቱን ነገር አውቆና



www.ethiopianortodox.org

አምኖ ጸሎቱ « ጌታ ሆይ አስበኝ » የምትል ነበረች ። እንደዚሁ ሁሉ በሠራነው ኃጢአት ሳቢያ የሚከበን እና የምንሸከመው ሀፍረት እየከበደንም ሳለ ፤ በዚህ ሳቢያ በዚህ ምክንያት ነው የበደልሁት ብለን የምናቀርበው ምንም ሰበብ እና ምክንያት የሌለን ሆነንም ሳለ ነገር ግን ከእኛ ኃጢአት እና ግፍ የሚበልጥ በሆነው በእርሱ ፍቅርና ምሕረት ስለምንተማመን በገነት ከእርሱ ጋ እንደምንሆን የሚያስተማምን ቃል ኪዳን እስክንቀበል ድረስ «ጌታ ሆይ አስበኝ  እያልን መጸለያችንን » አንተውም፡፡

ጌታ ወንበዴውን በገነት ትሆናለህ የሚል ቃልኪዳን ሰጥቶ ብቻ አልተውውም፤ በገነት ከእርሱጋ እንደሚሆን ጭምር ድርብ ቃል ኪዳንን ሰጠው እንጂ፡፡ በገነት መሆን መልካም ነው ። በገነት ከመሆን የተነሳ ከሚገኘው ነገር ሁሉ ብልጫ ያለው ጸጋ ደግሞ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር መሆን ነው፡፡

በእውነት ገነት ያለ ክርስቶስ ምንም አይደለችም፤ ደስታም አይገኝባትም፡፡ እውነተኛው ደስታ ከክርስቶስ ጋር መሆን ነውና ። እግዚአብሔር በልጆቹ መሀል በተገኘ ጊዜ እነርሱ የፍቅሩን፣ የአብሮነቱን፣ አባትነቱን እና የቸርነቱን ጣዕም የሚያገኙ ይሆናሉ፡፡ በዚያም ደስ ይሰኛሉ፡፡ ስለዚህ ገነት ትሰጠኝ ብለህ አትለምን ከእግዚአብሔር ጋር መሆንን፣ እርሱን ራሱን ማግኘትን ፤ ይህንን ለምን እንጂ፡፡ ከእርሱጋ መሆንን እና ሐሴት የሚያጎናጽፍ ገጹን መመልከትን ተመኝ፡፡

ፊትህን እሻለሁ፣ ፊትህን ከእኔ አትሰውርብኝ —— እያለ ዳዊት መናገሩ እንደምን እውነት ነው! ከወንበዴው ታሪክ እጅግ ደስ የሚያሰኘኝ ነገር በምድር ከጌታችን ጋር (እንደ ፊቃዱ) ያልተመላለሰ፣ አካሄዱ ከእርሱ ጋር ያልነበረ ሆኖ ሳለ በገነት ግን ከጌታ ጋር የመሆንን ቃልኪዳን ማግኘቱ ነው፡፡ እንዲህ ያለ ቸርነት ለእርሱ መደረጉ ዕጹብ ነው ! ።

ከጌታ ጋር ያሳለፉት ጥቂት ሰዓት ፍጻሜ ለሌለው ዘለዓለማዊ ቆይታ ከጌታ ጋር የመሆንን ጸጋ ልታጎናጽፈው የምትበቃው ሆነች፡፡ ዋናው ሀቅ በኒህ ጥቂት ሰዓታት ያለፉት ጥልቀት ባለው ፍሬ ነገር መሆኑና በዚያች ሰዓት እርሱ ያደረገው ሁሉ ጌታን ዘልቆ እስኪሰማው ደረስ እጅግ ልባዊ ፣ ኃይል ክንውን የነበረ መሆኑ ነው ።



www.ethiopianortodox.org

ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር በመጸለይና በመለመን የፈጀኸው ጊዜ ርዝመት ቢበዛና ቢያንስ በራሱ ምንም ትርጉም የለውም ። ጥያቄው ስትጸልይ ስሜትህ ምን ያህል ጥልቅ ፣ ምን ያህል ልባዊ ነበር የሚለው ነው በጥልቅ ስሜት ከልብ የወጣ ቃል ታላቅ ውጤት አለው ። እንዲህ ያለውን ልባዊ ቃል አውጥተህ ተናገረው፤ ከእግዚአብሔር መንበር ደርሶ የሚሰማ ቃል ይኖርህ ዘንድ ከእርሱ ጋር የሚኖርህን አካሄድ፣ አኗኗር፣ ጥልቀት ያለው አድርገው።

## ድርሳነ-ዘአባ ሕርያቆስ

### ኤጲስ ቆጶስ ዘሀገረ ብህንሳ በአንተ ሐዘና ለድንግል

*ልመናዋ ክብሯ ለዘለዓለሙ በኛ ይደርብንና ስለ እመቤታችን ስለ ድንግል ማርያም የብህንሳው ኤጲስ ቆጶስ የሚሆን አባ ሕርቆስ የተናገረው ድርሳን።*

ጽኑ ልቅሶ ይዟት ነበር ልጇን ለማየት ስለ አልቻለች በዮሐንስ ቤት እንደገና ወደ ለቅሶዋ ተመለሰች። ዮሐንስ ወደ ቀራንዮ ይዘህኝ እንድትሔድ እማጸንሃለሁ ወደ ጎልጎታ ከእኔ ጋር እንድትሄድ እማጸንሃለሁ ሌባ ሲሰቀል ወንበዴም ራሱን ሲቆርጥ አላየሁም አገሬን ማደሪያዬን ትቼ ልጄ ወደ ተሰቀለበት እሄዳለሁ። ልጄ የተሰቀለበትን ቦታ ለማየት እወዳለሁ ልጄ ሆይ ከደቀመዛሙርትህ አንድ እንኳ ከአንተ ጋር የቆመ ስለአንተም አንድ ቃል የተነገረልህ የለም ። ልጄ ከእናቱ ኅዘን ለተወደደ ልጇ የምታዝነው ኅዘን ልዩ ነው ። የወዳጅም ኅዘን ለወዳጅ ልዩ ነው ።በተወዳጅ ልጇ መከራም እናት የምትጨነቀው ጭንቅ ልዩ ነው ። ማዘንማ ወዳጅ ያዝናል የእኔ ኅዘን ግን ከዚህ ሁሉ ልዩ ነው ። ከኢየሩሳሌም ሰዎች ሁሉ ኅዘን ይበልጣል በእኔ ዘንድ ከተሰበሰቡት ኅዘን ;የእኔ ይበልጣል እያለች ታለቅስ ጀመረ ።

ዮሐንስም ልቅሶዋን ለማስተውና እንዲሁም ከልቅሶዋ መረጋጋት እንዳልቻለች ባየ ጊዜ ተነሺ እንሂድ አላትና ከዮሐንስ ቤት ወደ ቀራንዮ ሄደች በመንገድ የሚያዩዋት ሁሉ እንደዚህ በመጣደፍ የምትሔድ አይተን አናውቅም እያሉ ያደንቁ ነበር። ዮሐንስም የጌታ ደቀመዝሙር መሆኑን የሚያውቁ ይህች እናቱ ትሆናለች መልኳም የእሱን መልክ ይመስላል ይሉ ነበር። ሰሎሜም በኋላዋ ትከተላት ነበር። ሌሎችም ሴቶች የኀዘን ልብስ ለብሰው ተከትለዋት ነበር፡ እመቤታችን ወደፊት ከመገስገስ በስተቀር ወደቀኝም ወደግራም አታይም ነበርና ጎልጎታም በደረሰች ግዜ ከከተማዉም ከገጠሩም የተሰቀለዉን



www.ethiopianortodox.org

ለማየት ህዝብ ተሰብስቦ ስለፋሲካዉም በዓል ከየነገዱ የተሰበሰቡ ብዙ ሰዎች ነበሩ። የተደረገዉንም ተአምራት ለማየት የተሰበሰቡት እርስ በእርሳቸው ይጋፉ ነበር። ከተሰበሰቡትም ሰዎች የዚህን ሰው ሞት ብዙ ጊዜ ሲመኙ የነበሩ ዛሬ በግፍ ገደሉት ነገር ግን የእውነት ፍርድ ባይኖር ነው የሰቀሉት ይሉ ነበር። እመቤታችን ግን ከኃዘኗ ጽናት ከሕዝቡም ብዛት የተነሳ ቀና ብላ ሰዉ ለማየት አልቻለችም። ዮሐንስን የምወደዉ ልጄ ወዴት ነዉ ያለዉ እንዴት አድርጌ ነዉ ላየዉ የምችለዉ አለችዉ። ዮሐንስም በተሰበሰበዉ ሰዉ መካከል ዓይንሽን ቀና አድርገሽ ወደ ምሥራቅ ተመልከች በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ታይዋለሽ አላት ዓይንዋን ወደ ላይ አቅንታ በተመለከተች ጊዜ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ አየችዉ። በሰዉም መካከል እየሔደች ከአጠገቡ ደርሳ ቆመች በመከራ ሲሰቃይም አየችዉ። ጌታም የእናቱን መከራና ኀዘን ባየ ጊዜ ወደ ዮሐንስ ተመልክቶ «ይች እናት ትሁንህ» አለዉ። እሷንም «ይህ ልጅሽ ይሁንሽ አላት»

ዮሐንስም 'ወደቤታችን እንሒድ' ብሎ እመቤታችንን ለመናት እመቤታችንም እባክህ ተወኝ ለልጄ ላልቅስለት ብቻዉን ነዉ ወንድም እህት የሌለዉ አንድ ብቻ ነዉና። ልጄ ሆይ ይህ በአንተ ራስ ላይ የተደፋው የእሾህ አክሊል በእኔ ራስ ላይ በሆነ ለአንተ በተጨነቅሁልሁ እያለች ታለቅስ ጀመር። ዮሐንስ ሆይ ተወኝ የልጄን ፊት አይቼ አልጠገብኩትምና ልጥገበዉ ለዛሬ በቀር ላየዉ አልችልምና። ይህ ቦታ ኢዮብ በመከራ ጊዜዉ ያለቀሰበትና ያዘነበት ነዉ። ይህ ቦታ የደካሞች ሁሉ መጠጊያ ነዉና እኔም እናት የሌለኝ ስለሆንኩ ከዚሁ እየወደቅሁ እየተነሣሁ ላልቅስ እያለች ከማልቀስ በቀር ምንም አትመለከትም ነበር። አብረዋት ያሉ እነ ሰሎሜ እነ ዮሐንስና እነ ማርያም መግደላዊት ያነሷት ይድግፏት ነበር። በሴቶች መካከል የምታለቅሰዉ እጅግ ያሳዝን ነበር። እነርሱም የእሷን ለቅሶ እያዩ ያለቅሱ ነበር። ከአይሁድ ወገን የሆኑ ሴቶች ግን ይገዳደሯት ነበር። ስታለቅስ እያዩ በአንቺ ልጅ ምክንያት ልጆቻችን እየተነጠሉ ሞተዋል የኛስ በቀላችን ተመለሰልን እያሉ ይዘባበቱባት ነበር። ከሔሮድስ ጋር የነበሩ ትልልቅ ሰዎች ሁሉ ሔሮድስ እንደጠላዉ የሚጠላበትን ነገር ይፈልጉ ነበርና ጲላጦስ ሚስት ልጆቻቸዉን ስላዳነ ጌታን ይወዱት ነበር። ጲላጦስ ግን የአይሁድን ፈቃድ ለመፈጸም ሲል ከዳኝነት ዉጭ በሆነ ነገር ገርፎ ስቀሉት ብሎ ሰጣቸዉ። ወደቀድሞ ነገር



www.ethiopianortodox.org

እንመለስና ዳግመኛ ዮሐንስ እመቤታችንን ወደ ቤት እንሂድ ብሎ ለመናት፡፡ እሷ ግን ከኃዘኗ ብዛት የተነሳ ልጄ እሰናበትሃለሁ እያለች እየጮኸች እያለቀሰች ዕራቁትህን መሰቀልህን የእሾህ አክሊል መቀዳጀትህን የተተፋብህን፤ በሁለት ወንበዴዎች መካከል መሰቀልህን ልብስህን ጠላቶችህ መከፋፈላቸዉን ፤ ይህን የመሰለዉን ሁሉ የፈጸሙብህን እያሰታወስኩ እሰናበትሃለዉ ብላ ተመልሳ ዮሐንስ ቤት ደረሰች፡፡ ከኀዘኗም ጽናት የተነሳ እንቅልፍ አታሽልብም ነበር፡፡ ልመናዋ በረከትዋ በሁላችን ልይ ይደርብን ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

## ድርሳነ ዘቅዱስ ዲዮናስዮስ

## በረከቱ የሃሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

አቴና በሚባል ሀገር ዲዮናስዮስ የሚባል በሰማዕትነት የሞተ አንድ ሰዉ ነበረ፡፡ እሱም በዕዉቀቱና በአነጋገሩ ከሰዉ በላይ የሆነ ከንጉሡ አማካሪዎች አንዱ ነበረ፡፡ ከፈላስፋ ሹማምንትም አንዱ ነበር፡፡ ኃላ ግን ቅዱስ ጳዉሎስ አስተማረዉና አጠመቀዉ፡፡ ከድርሳኖቹም አንዱ ክብር ምስጋን ይግባዉና የዓለም መድኃኒት የሚሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተሰቀለበት ስለ ዕለተ ዓርብ ነዉ የፈላስፎች ዓለም ስለነበረ ይህ ቅዱስ በፍልስፍናዉ ቦታ ከፈላስፎቹ ጋር በወንበር ተቀምጦ ሳለ በቀትር ጊዜ ፀሐይ ጨለመ ምድርም ተነዋወጠች አሕዛብም ሁሉ ደነገጡ ፈሩ ዲዮናስዮስን ምክንያቱን ግለጥልን ብለዉ ለመኑት፡፡ የፍልስፍናዉን መጽሐፍ ሁሉ እየገለጠ ቢመለከትና ቢመረምርም ሁሉም ከቦታዉ ሳይናወጥ አገኘዉ፡፡ ባሕርም ታዉኮ እንደሆነ ብሎ ቢመለከት ደህና ሆኖ አገኘዉ፡፡ አርስጣላብ የሚባል የፍልስፍና መጽሐፍ አዉጥቶ ቢመለከት ሰማይና ምድርን የፈጠረ አምላክ ከዙፋኑ ወርዶ ወገኖቹ በጠላትነት ተነስተዉ ሰቀሉት ሲል አገኘዉ፡፡ በዚህ ጊዜ ፊቱን እየፀፋ ብዙ አዘነ፡፡ ከአደባባዩ ያሉት ምክንያቱን ግልጽልን አሉት፡፡ ይህንኑ ገለጸላቸዉ፡፡ እንርሱም አዘኑ ፍርሃትም አደረባቸዉ ከዚህ በኃላ ኡሲሞስ የሚባለዉ ደቀመዝሙሩን የተደረገዉን ነገርና ቀኑን ሰዓቱን የወሩንም ስም ዓመተ ምህረቱን እንዲጽፍና እንዲያስቀምጥ አዘዘዉ፡፡ ጽፎ አኖረዉ፡፡ በጣዖታቱም በር ላይ ይህንን ጽፎ ተወው፡፡ ከአስራ አራት አመት በኃላ ጳዉሎስ እያስተማረ ወደ አቴና መጣ፡፡

ከሰማይ ጌታ ወረደ፤ ተወለደ፤ ሰዉ ሆነ፤ አስተማረ፤ ተሰቀለ፤ ሞተ፤ ተነሳ፤ ዐረገ እያለ ይሰብክ ጀመረ፡፡ የአቴና ሰዎች ትምህርቱን



www.ethiopianortodox.org

ሰምተዉ ሄደዉ ዲዮናስዬስን እኛም አባቶቻችንም ሰምተነዉ የማናዉቀዉን አዲስ አምላክ ያስተምረናል ብለዉ ነገሩት፡፡ ዲዮናስዮስም ጳዉሎስን ምን እያልክ ታስተምራለሁ አለዉ ይህንኑ ገለጠለት፡፡ ያን ግዜ ዲዮናስዮስ ደቀመዝሙሩን ያንን የጻፍከዉን አምጣ አለዉና አምጥቶ ቢያየዉ ወሩም ቀኑም ዓመተ ምህረቱም የተደረገዉ ተአምራት ልክ ሆነ፤ ሰዓቱም ስድስት ሰዓት ሆነ እንዴት ይሆናል አለዉ፡፡ ጳዉሎስም በዚህ አትጠራጠሩ የሞቱት ተነሥተዉ ወደ ዘመዶቻቸዉ ሄደዋል ይህም ብቻ አይደለም በሲኦል ያሉ ነፍሳትን በሰይጣን ምርኮኝነት ያሉትን መድኃኒታችን ክርስቶስ አዉጥቷቸዋል ብሎ አስረዳቸዉ፡፡ ያን ግዜ አመኑ፡፡ ተጠመቁ፡፡ ለጳዉሎስም የአክብሮት ስግደት ሰገዱለት ጳዉሎስ ዲዮናስዮስን ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ሾመላቸዉ፡፡ ዲዮናስዮስም ብዙ ተአምራት አደረገ፡፡ የቤተክርስቲያንን ሥርዓት ተረጎመ፡፡ በመጨረሻም አረማዉያን በሰይፍ መተዉት ሞተ፡፡ የዲዮናስዮስ ረድኤቱና በረከቱ በሁላችን ላይ ይሁን አሜን፡፡

*በአብ ስም አብን ወላዲ በወልድ ስም ወልድን ተወላዲ በመንፈስ ቅዱስ ስም መንፈስ ቅዱስን ሠራጺ ብዬ ሦስትነትን ለመግለጽ ሦስት ብልም በመለኮት አንድ አምላክ ብዬ በስሩግ ኤጲስ ቆጶስነት የተሾመ አባ ያዕቆብ የደረሰዉ ድርሰት ይህ ነዉ እላለሁ፡፡*

የእግዚአብሔር ወዳጅ ስለሆነ አባታችን ስለ አብርሃም ልጁን ይስሐቅ ለመሥዋዕትነት ስለማቅረቡና እግዚአብሔር በበግዕ እንዴት እንዳዳነዉ የሚናገር ነዉ፡፡ እግዚአብሔር አንድ ያድርገን አሜን፡፡

የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ወደ ልቦናዬ ምስጢርን ሊያዉቅ ይወዳልና ለሚሰሙ ልገልጥላቸዉ እወዳለሁና እዉቀትን ስጠኝ፤ የሰሙትንም ድስ ይላቸዉ ዘንድ የአንተን ነገር እናገር ዘንድ አሳዛኝ የሆነ ሞተህ ይቀሰቅሰኛል፡፡ ድርሳንህን በሚገባ እናገር ዘንድ ዕዉቀትን ግለጥልኝ ደካማ የሆነ አንደበቴ የአንተን ነገር ቢናገር ይፈቅዳል፡፡ የሞትህን ቀን ሊያይ እንደወደደ ፤ እዉነትም እንደመሆኑ የሞትህን ቀን አየ እኔም ደካማዉ የሠራሁትን ልናገር እፈልጋለሁ፡፡ አብርሃም ምሥጢርህን አይቶ ደስ እንደ አለዉ፤ የሞትህ ምሳሌ ተገልጾለታልና



www.ethiopianortodox.org

ዳግመኛም በቸርነትህ ስጦታ ደስ አለዉ በገለጥህለት ጊዜ ወልደ እግዚአብሔር ሆይ ከአንተ የተገኘዉ ታላቅ ምሥጢር ነዉ። በግዕ የታሰረበት ዕፅ የጎልማሳ የይስሐቅን አንገት በፊታ ጊዜ ድንቅ ምሥጢር ተገለጠ። ሽማግሌ አብርሃም የእግዚአብሔርን ቀን ሊያይ ተመኝቷልና በጌታችን መድኃኒት እንደምን እንደሚገለጽላቸዉ ማወቅን ልቤ በዚሁ ነገር በተቃጠለ ጊዜ ከምስጋና መልካም ምሥጢር ተገለጸ። እንግዲህስ እንዲህ እላለሁ አብርሃም እንዴት በምን አኳኋን ይህን ቀን አየ? እንዴትስ ደስ አለዉ? ያን ጊዜ የይስሐቅ ነገር እንደሌባ ሹልክ ብላ በጥልቅ ልቡና ትገባለች። በተነገረችስ ጊዜ ምን አንደበት እሷን ሰዉሮ ሊናገር ይችላል የይስሐቅ ምሳሌነትና በመጨረሻም የሚደርሰዉን ነገር ከመናገር እንቆጠብ ተወኝ፤ ልትነግር የሚገባትን መሥዋዕትነት ገልጬ ልናገር መጨረሻዉንም እነግርሃለሁ አሁንስ ስለአብርሃም የወልድን ነገር መናገር ተገለጠ እግዚአብሔር አብርሃም ብሎ ጠራዉ። አብርሃምም እኔ አለሁ ጌታዬ አንድ ልጅህን ወስደህ እኔ በማሳይህ ተራራ ሠዋዉ አለዉ። እግዚአብሔር ይስሐቅን እንዲሠዋለት ፈልጎ አይደለም ለወልድ መሥዋእትነት ምሳሌ እንዲሆን ነዉ እንጂ ይስሐቅን የእሱን ቀንሼ እንዳስቀር ህሊናዬ አይፈቅድልኝም። ሥራዉን ገልጬ እንድናገር ይገፋፉኛልና። የዚህም ትርጓሜ የጌታችን ሞት ነዉ። ዳግመኛም የአገልጋዩ የይስሐቅ ነገር የመካን ልጅ ለእሱ ብቻውን ሲሆን ልጅህን ወስደህ ሰዋልኝ ባለው ጊዜ ይህ ነገር ታላቅ ምሥጢር ባይሆን ኖሮ አይሆንም ሳይል ለምን ይሰዋው ነበር ልጁስ አባቱን እሺ ብሎ ለምን ይሄድ ነበር።

አስቀድሞ ለወልደ እግዚአብሔር መሥዋዕትነት ምሳሌ ሆኖ ነው እንጂ። እግዚአብሔር አብርሃምን በዚህ ፈተነው። መጻሕፍትም ይህንኑ ይናገራሉ። ይህንን የምታስተምር የዚህን ጥልቅ ምሥጢሩን ለመረዳት ሞክር እግዚአብሔር አብርሃምን ሊፈትነው ለምን ፈለገ? የአብርሃምን ደግነት የሚያውቅ ከሆነ ለምን ወዳጅ አደረገው? ረቂቅ የሆነ ምሥጢርን ለመግለጽ ስለፈለገ ነው እንጂ የይስሐቀን ምሳሌነት የፈለገው። ስለዚህ ይህን አድርጎ አብርሃም የወልደ እግዚአብሔርን የሞቱን ዕለት ሊያይ ይፈልግ ነበርና። ይስሐቅም ስለዚሁ ታገሠ። በአንድ በአብ ልጅ ምሳሌ ይስሐቅ ሞትን ታገሠ። አብርሃም የስቅለትን ምሳሌ አይቶ ደስ ይለው ዘንድ እንዲህ ከሆነ አብርሃም የአምላክን



www.ethiopianortodox.org

ምሥጢራት አወቀ ማለት ይቻላል፡፡ እውነተኛውን ምሥጢር ከጊዜው ሳይደርስ አየ ብለህ አስተዉል፡፡ መንገዱ እንዴት እንደተቃናለት ተመልከት፡፡ አብርሃም ከእግዚአብሔር ልጅህን ሰዋልኝ የሚል ትእዛዝ ተሰጠው እርሱም ለጌታው የሚሰጠው መልስ ነበረው፤ መልስ መስጠት ቢፈልግ ኖሮ በተሰጠው ሊመልስ ይገባው ነበር፡፡ ምንም ቃል ሊመልስ አልፈቀደም እንጂ በዚህ ልጅ ዘርህ ይበዛል በለህ ባርከህ ሰጥተኸኛል ፤ መሥዋዕት ካደረግሁት በምን ይበዛል? ቃል ኪዳንህም ተሻረ አልሠራም፤ ብልህ ትእዛዝህን ማፍረሴ ነዉ ብሎ መመለስ ይቻል ነበር፡፡ ዳግመኛም አቤቱ ላንተ ዘርህ ይበዛል ብለህ ተስፋ ሰጥተኸኛል፤ አባት ልጁን ሰዉቶ ዘር የበዛለት በየትኛዉ ዘመን ነዉ? እስኪ አስረዳኝ ብሎ ሊጠይቅ ይችል ነበር ፡፡ አብርሃም ግን ከነዚህ ቃሎች አንድም አልተናገረም ፡፡ መልስ መስጠትም አልፈለገም ፡፡ አብርሃም ጌታውን ስለወደደና ስላመነ ከጌታው ጋር መከራከር አልፈለገም፡፡ ይስሐቅም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነውና የተሰጠውን ትዕዛዝ በአንክሮ ታግሶ ተቀበለ ይችን ላያትና ልደሰትባት የምፈልጋት ናትም አለ፡፡ እሱ ለረቂቅ ምሥጢር ምሳሌ ነውና «ለልጅህም አትዘንለት እኔም ለምወደው ልጄ አላዝንለትምና ልጅህን ሰዋው እኔም ከብዙ ዘመን በኋላ እንዲሁ አደርጋለሁና፡፡ ለአንድ ልጅህ አትዘን እኔ ለአንድ ልጄ እንደማላዝን እሱም አምላክህ ነው» ዳግመኛም አስተውል ልጅህ ለመሥዋዕት በቀረበ ጊዜ አትጠራጠር የክርስቶስ ምሳሌነቱን እንዳታስቀር ሰይፉን ለመሥዋዕት በእጅህ ባነሣህ ጊዜ አትሸበር አትፍራ ምሳሌነቱን እንዳታስቀር ሰይፉን ለመሥዋዕት በእጅህ ባነሳህ ጊዜ አትሸበር ፣ አትፍራ ምሳሌነቱን እንዳታስቀር ሰይፉን ለመሥዋዕት በእጅህ ባነሳህ ጊዜ አትሸበር ፤ አትፍራ ምሳሌነቱን አንዳተጎድል እሱንም በሠዋህ ጊዜ በልቡናህ ኃዘን እንዳይደርስ ተጠንቀቅ፡፡ ምሳሌነትህ አንዳይቀር፡፡ ስለዚህ አብርሃም ይስሐቅን ሊሠዋው ይዞት ሲሄድ ደስ እያለው ሄደ፡፡ ጎዳናውንም በፍጥነት ለመፈጸም ቻለ፡፡ ለሚስቱም ለሣራም አልነገራትም፡፡ በዕድሜ የደከመች ናትና እንዳታዝን ለአንድ ልጇም የምትሳሳ ናትና በእሱና በጌታው መካከል ያለውን ምሥጢር ለአንድም ሰው አልገለጠም፡፡ አብርሃም ጌታው እንዳዘዘው ፈጥኖ ሄደ፡፡ ከቤት በሚወጣበት ጊዜ ምሥጢር አልነገራትም አለመንገሩም መልካም አደረገ ፤ የደከመች ባልቴት ናት አእምሮዋን እንዳታጣ እናቷ ሔዋንን ያገኛት እንዳያገኛት ከመካን እናት ደብቆ



www.ethiopianortodox.org

ይዞት ሄደ፡፡ አሽከሩን ልኮ ና እንሂድ ብሎ ይዞት ሄደ ለአሽከሮቹም ምስጢሩን አልገለጠላቸውም፡፡ እግዚአብሔርና አብርሃም ብቻ ናቸው የሚያውቁት አባቱ ይስሐቅን ለመሥዋዕት ይዞት ሲሄድ አላዘነለትም፡፡ የታዘዘውን ለመፈጸም ብቻ ሄደ እንጂ ራሱን የሚሠዋበትን እንጨት አሸክሞ ይዞት ሄደ ፤ የሚሠዋው ካህን እርሱ ብቻውን ይዞት ሄደ፡፡ ወቀለምቱን ሳል ሳል አድርጎ አንድ ልጁን ለመሠዋት ተዘጋጀ፡፡ አብረው ያሉት አሽከሮቹ ለመንገድ መቸኮሉን አይተው አደነቁ፡፡

ወዴት እንደሚሄድ ስላልነገራቸው ምክንያቱን ሊጠይቀው ለእነሱ የደፈረ የለም፡፡ በመንገዱም ሁሉ ሲሄድ የአምላክ ምስጢር ይታየው ነበር፡፡ የልጁ የይስሐቅም የአንድ ልጁም ሞት አላሳዘነውም፡፡ ልጁን ለመሠዋት ይዞ ሲሄድ ልቡ በኃዘን የማይሸበር ማነው? ምንም ልቡ እንደ ድንጋይ የጸና ቢሆን እንዴት አያዝንም? ይስሐቅም ለአባቱ ሕይወት የተሞላ ነገር ነገረው፡፡ እሱ ሊሠዋው ይዞት መሄዱን ወደየትም እንደሚሄዱ አያውቅምና፡፡ ስለዚህ ከአባቱ ጋር ባለመፍራት ይነጋገር ነበር፡፡ አባቱ ግን አስሮ ለመሠዋት ተዘጋጅቶ ነበር፡፡ ይስሐቅም ከእሱ ሌላ የሚሠዋው ያለ ይመስለው ነበር ፤ ነገሩን አያውቅምና ነበርና አባቱ ምን እንደሚያስብ እንደማያውቅም ይሰማው ነበር፡፡ ይስሐቅ በደስታ ይጓዝ ነበር፡፡ ይህ ምሥጢር የተሰወረ ነበርና፡፡ ሲሄዱም በችኮላ ነበር፡፡ ሌሎች መምህራንም ሦስት ቀን እና አንድ ብዙ ምዕራፍ እንደተጓዘ ይናገራሉ፡፡ የአብርሃምን ድካምና ትዕግሥት እስኪመለከት ጎልማሳ ይስሐቅ ግን በጎዳናው ሁሉ ከአባቱ ጋር መነጋገሩን አልተወም፡፡ ወዴት አገር እንሄዳለን አላለውም የሚሠዋው በግ ወዴት አለ? እያለ ይጠይቀው ነበር እንጂ፡፡ እንዲሁም ስለመንገዱ ርቀት አባቴ ስንት ቀን ነው የምንጓዘው? መቼ ነው የምንደርሰው? እንዲህ በችኮላ የምንሄደውስ ወደኛ የመጣና ከነገሥታት ና ብሎ ልኮብሃልን? ወይስ ከአባቶችህ አምላክ ተጠርተህ እንደሆነ፡፡ የምንሄድበት ሥራ ግን የሕይወት መንገድ መስሎ ይታየኛል ስለዚህ ጥቅም ለማግኘት በሥራህም ፣ ባሳብህም ስትቸኩል አይሃለሁ፡፡ አካሄድህም እንደ ፏፏቴ መጨረሻ ናት፡፡ ይስሐቅ ይህን የሚጣፍጥ ንግግር ካባቱ ጋር ይነጋገር ነበር፡፡ አብርሃም ግን ለጠየቀው መልስ እንዳይሰጥ ሌላ ነገር እያመጣ ይናገር ነበር፡፡ የጠየቀውን ነገር ያልሰማ እየመሰለ እንዲህ አድርጎ በድካም ሦስት ቀን ተጓዘ፡፡ ከመሥዋዕቱ በቀር

የሶስት ቀን ጎዳና በተፈጸመ ጊዜ እግዚአብሔር አብርሃምን ተናገረው የዓለም ሁሉ መዳን ወደሚፈጸምበት ወደዚህ ተራራ ውጣ በመሰዊያውም ላይ ሕያውና ምውት ሆኖ የቀረበ ንጹሕ መሥዋዕትና ቁርባን ያለመጥባሕት የተሠዋ ተመልከት ፤ ማህያዊ የወልድን ዕለት ተመልከት አንተም ዛሬ ልጅህን በመሠዋት ግለጠው ፤ ይህችን ነገር ቀርበህ ተረዳት እወቃት ፤ ከዚህ በኋላ ባንድነት ያሉትና የሚፈጸሙትን ነገሮች ያየህ ምሳሌ ትሆናለህ። ይህን ምሳሌ ና ተመልከት ትልቅ ምሥጢር የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌነት ተፈጽማለች። የመንገድህ ፍጻሜ ይህ ነው። የመንገድህ ማረፊያ ወደዚች ቦታ የቅርብ ምስክሮችን ትረዳ ዘንድ ይህን አልፊህ እንዳትሄድ እወቅ በዚህ ቦታ የንጽሕ የጌታ ደም ይፈስበታል። አንድም ምሥጢር የሚሰጥበት ደም አፍስበት ከዚህም በማመን ሄደ ይሥሐቅ ከአብርሃም ጋር የወጣበት ተራራ ጎልጎታ ነውና መስቀሉ ከተተከለበት ቦታ ይስሐቅ ታሰረበት። በግዕም የታሰረበት ወልደ እግዚአብሔር የተሰቀለበት ዕፅ ነው። የይስሐቅ እግር በታሰረበት ወልደ እግዚአብሔር እጅንና እግሩን ተቸነከረበት። ለይስሐቅ መስዊያ ወቅለምት ለጌታ መውጊያ ቀኖት ተሳለበት። ለአሽከሮች ከጌታው ቀድሞ መንገድ መጥረግ ይገባልና። ጌታ የሚመጣና ስለ ኃጥአን መሥዋዕት የሚቀርብ ነውና። አብርሃም ሲጓዝ በዚህ ተራራ ላይ ይህን ምልክት አየ። ይስሐቅ መሥዋዕትነቱን ሳያውቅ እንደመጣ አብርሃምም በዚህ ተራራ ላይ ምልክት አየና ወደ እሱ ሄደ። ከዚህ በኋላ በዚህ ተራራ ላይ ምሥጢሩ የሚፈጸምበት መሆኑን አወቀ። እንዲህ እንደተናገርነው የሚሄድበትን ተራራ ያሳየው ማነው? እግዚአብሔር ልጅህን እኔ በማሳየህ ተራራ ላይ ሠዋው ብሎታል እንጂ እገሌ በሚባለ ተራራ ላይ ሠዋው አላለውምና። ስለዚህ አልፎት እንዳይሔድ ገና ሳይደርስ ምልክት አሳየው። ሌሎቹን ተራሮች አልፎአቸው እንደመጣ። ይስሐቅን በጎልጎታ ይሠዋው ዘንድ ክርስቶስ በመሠዊያው ከመስቀሉ አስቀድሞ አብርሃም ሦስቱን ቀን ሲጓዝ መቼ ይሆን ? እንዴት እደርስ ይሆን ? የሚያሳየኝ እያለ በተስፋ ይጓዝ ነበር። ጻድቅ አብርሃም ወድ መቃብር ሦስት ቀን የማደሩን ምሳሌ ይፈጽም ነበር። ጌታ ሞትን በሦስተኛው ቀን ድል ነሥቶታልና። ይስሐቅም በተጓዘ በሦስተኛው ቀን አባቱ ሠዋው። ምሳሌው ይፈጸም ዘንድ ከሦስት ቀን በኋላ እንዲነሳ በሦስተኛው ቀን ይህ ምልክት ታየው። ከዚህ በኋላ አሽከሮቹን ከዚህ



www.ethiopianortodox.org

ቆዩ እኔና ልጁ ከተራራው ላይ ጸሎት አድርገን እስክንመለስ ድረስ ከዚህ ቆዩ አላቸው፡፡ ከጸለይን በኋላ ወደ እናንተ እንመለሳለን፡፡ አብርሃምም ያስብ ኖሯል፡፡ ልጁ በሕይወት እንዲመለስ የተጠራጠር ይመስል፡፡ ስለዚህ አሽከሮቹን ከተራራው በታች ቆዩ አላቸው፡፡ ወይስ ድኖ መመለሱን ትንቢት መናገሩ ነው ወይስ ይስሐቅ እንዳይፈራ ማረጋጋቱ ወይስ ተሠውቶ እግዚአብሔር ያስነሳልኛል ብሎ ማመኑ ነው? የሚናገረው ሁሉ የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ ነውና፡፡ እንዴት አውቆ እንመለሳለን አለ፡፡ እሱ የሚሠዋበትን እንጨት አሸክሞታልና፡፡ ይህን በምን አውቆ ለእግዚአብሔር ሰግደን እንመለሳለን አለ፡፡ ከእኛ ጋር ወደ ተራራው ሊወጡ አይገባምና መንገዳችን ወደ እግዚአብሔር ነው፡፡ አብርሃም በልቡ ወቅለምቱን ይስላል? ከአሽከሮቹም ለይቶ ከእሱ ጋር ወደ ተራራ እንዳንወጣ የከለከለን ለምንድን ነው? ወደሚሄድበት ቦታ ሁሉ ዘወትር ይዞት ሲሄድ ለእግዚአብሔርስ የሚሰግድስ ከሆነ የሚጸልይበትን ልብስ ለምን አለበሰም የሚሠዋስ ከሆነ የሚሠዋው በግ የት አለ? እያሉ ይወያዩ ነበር፡፡ ከእሱ በቀር ሌላ አይታይም ነበር፡፡ አብርሃም በኅልጎታ በተገለጠበት ምሥጢር አእምሮው ተመስጦ ነበር፡፡ መስቀልም በእጁ መካከል ይታየው ነበር፡፡ ስለዚህ ነው ከዚህ ቆዩ ብሎ የሸነገላቸው፡፡ ዳግመኛ የሚያስደስት ምሥጢር ብቻውን ለማየት ሰለፈለገ ነው በህሊናው ይስሐቅ የሚሠዋበትን ስለት ሲስል ሰውቶትም እንዲድን ተስፋ ያደርግ ነበር፡፡ ነገር ግን በምን ዓይነት እንደሚድን አያውቅም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ልጁን እንጨት እንዲሸከም ይዞት ወጣ፡፡ እሳቱንና መጥባሕቱን እሱ ይዞአል፡፡ የወልድ መስቀል ያን ጊዜ እንደተፈጸመለት አሁን አወቅን ተረዳን፡፡ ስለዚህ ይስሐቅ ምሳሌ፡፡ ከአሽከሮቹ አንዱን እንጨቱን ተሸክመህ አድርስህ ተመለስ ብሎ ቢያዘው ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን መስቀሉን ጌታ የመሸከሙ ምሥጢር አልፈቀደለትም እንደዚሁም ይስሐቅ የእሱን ምሳሌ ሆኖ የሚሠዋበት እንጨት ተሸክሞ ሄደ፡፡ የጌታ መስዋዕትነት ምሳሌ ይሆን ዘንድ የይስሐቅን መሥዋዕትነት አስቀድሞ አስፈጸመ፡፡ በይስሐቅ የተፈጸመው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሆነ ፡፡ የመድኃኒታችን የወልድ መታወቂያ እንዲሆን ታዞ የወልደ እግዚአብሔርን ሞት መሪ ሆኖ አስቀድሞ ሄደ፡፡ ይስሐቅም የተሰወረውን ነገር መጠየቅ ጀመረ፡፡ አባትህ ለሚፈጽመው ነገር የምትሄድ መሆኑን ጠይቀህ ተረዳ የሚል ሀሳብ ተንቀሳቀሰበት፡፡



www.ethiopianortodox.org

ይስሐቅ መጥባሕት ለማብረድ እንደተሳለ አየና ተመለከተ። መጥባሕቱን ከእሳቱ ጋር የተሸከመ አብርሃም ነው። አባቱ መጥባሕቱን አዘጋጅቷል። የሚሠዋው በግ የለም አለና አባቴ ብሎ ጠራው። አብርሃምም ልጄ ሆይ ምንድን ነው**?** ብሎ መለሰለት። ከዚህ በኃላ አባቶች በልጆች በሚያደርጉት በመታዘዝ የነጋገሩ ጀመር። ልጄ ምንድነው ያልህ? ባለው ጊዜ አባቴ አንጨቱም እሳቱም አለ ሰይፍም ተሳለ የሚሠዋው በግ የት አለ ? ከእኔና ከአንተ አንዳችን እንደሆን ነው እንጂ። ዳግመኛም አሳቱ አለ የሚጨሰው መስዋዕቱ የለም አንተ በሚሰዋው ካህን አምሳል ተዘጋጅተሃል የምትሰዋው መሥዋዕት ግን የለም። እኔም ታቀርበኝ እንደሆነ ነው እንጂ። ከዚህ ለመሥዋዕት የሚቀርብ ላም ፤ በግ የለም እኔም መሥዋዕት አድርገህ ልታቀርበኝ ይመስለኛል። አልፈናቸው በመጣናቸው ተራሮች ላይ ላም ፤ በግ አላየሁም። እኔን እንደ በግ አድርገህ ልትሰዋኝ ትፍቅዳለህ መሰለኝ ከመንጋችን የምትሠዋው በግ መርጠን ይዘን እንድንመጣ ለምን አላደረግንም አለው። ይስሐቅም እንዲህ እያለ ለአባቱ ለአብርሃም የሚያሳዝን ነገር ይነገረው ነበር። እንዲህ እያለ ሲነግረው የልጁ መሥዋዕትነት አላሳዘነውም። የልጁን አነጋገር ሰምቶ መካን እናቱ በወለደችው ባንድ ልጁ የሚያዝን በኃዘን ልቡ የማይነካ ማነው**?** አብርሃም እየሰማ ልቡ በኃዘን አልተነካም። ከዓይኑ ስንኳ ዕንባ ወከክ አላለም። አብርሃም ለልጁ "**መሥዋዕት የሚሆነውን በግ እግዚአብሔር ይሰጠናል**" አለው። ይስሐቅም ለአባቱ ለአብርሃም የተናገረው ሁሉ ወልድ ሰው ከሆነ በኂላ ወልድ ለአብ የተናገረው ምሳሌ ነው። ይስሐቅ ለአባቱ መስዋዕት የሚሆነው በግ የት አለ**?** እንዳለው አባት ሆይ የሚቻል ከሆነ ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ እንዳለው ነው ሁለቱ የመለኮትን ነገር አንድ ሆነው ገለጡት። አብርሃም ለለበጉ ልጁ በጠየቀው ጊዜ መሥዋዕት የሚሆነውን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጅልናል ይህን እኔ የምፈልገው አይደለም ለእሱ ሁሉ ይቻላልና እሱ ይስጠኛል እኔ እንደታዘዝሁትና እንደነገሩኝ መሄድ ነው የሚገባኝ ገበሬ እግዚአብሔርን አምኖ ዘሩን ይዘራል፤ ፍሬ የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው አለው አብርሃም ከይስሐቅ ጋር ከተራራው ጫፍ በደረሰ ጊዜ መስቀል ከሚተከልበት ቦታ ከዚህ ቁም የሚል ምልክት ታየው። ትልቁ መሥዋዕት የሚሠዋው ከዚህ ነው። አብርሃምም ምልክት ወዳለበት ቦታ ቀርቦ እሳቱንና መጥባሕቱን ከተራራው ላይ



www.ethiopianortodox.org

አኖረ፡፡ መሥዋዕት ለመሸዋት የሚመቸውን ተመለከተ፡፡ በሃይማኖት የጸና አብርሃም በኀልጎታ ምሥጢር ይፈጸምበት ዘንድ ያለውን የመሠዊያ መሠረት ይሠራ ዘንድ ተዘጋጀ፡፡ ይስሐቅም አባቱ የሚሠራውን ባየ ጊዜ አንጨቱን ከትከሻው ላይ አውርዶ ከመሬት አሳረፈ፡፡ መሠዊያውንም ሲሠራ ባየው ጊዜ ድንጊያ እያቀረበለት አብሮ ይሠራ ጀመር፡፡ በፈቃዱ ለሚሞተው ለወልድ ምሳሌ ነውና መሠዊያው ሥራው በተፈጸመ ጊዜ እግዚአብሔር ፈጽም ሲል ተናገረው፡፡ አብርሃምም እንጨቱን በሠራው መሠዊያ ላይ ረበረበ፡፡ ከመሠዋት በቀር ሥራውን ሁሉ ፈጸመ፡፡ ይስሐቅም የሚሠራውን ቆሞ ይመለከታል፡፡ እንዴት አድርጎ እንዲሠዋ፡፡ "አባቱ እኔን ልትሰዋኝ የምትፈቅድ አንደሆነ አነሆ ከፍቃድህ አልወጣም እኔ በአንተ እጅ ውስጥ ያለሁ ነኝና የወደድከውን አድርግ" ይስሐቅ ከአባቱ ጋር ተነጋገረ በዚህ ጊዜ ሸሽቶ ለማምለጥም ይችል ነበር ጎልማሳ ነውና ሕፃን ወይም ሽማግሌ አልነበረምና፡፡ ነገር ግን ጸጥ ብሎ ራሱን ዘለፍ አድርጎ ታሰረ እጁን የኋሊት ታስሮ ሲወድቅ አልተፈራገጠም፡፡ ራሱ በፍቃዱ በይታሰር ሽማግሌ አብርሃም ይሰሐቅን ለማሰር ባልቻለም ነበር፡፡ በፈቃዱ  የሚሠዋ የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ስለሆነ በፈቃዱ ራሱ ታሰረ እንጂ፡፡ የእውነት መሥዋዕት ምሳሌነቱን ይፈጸም ዘንድ ምሳሌው እንዳይጠፋ አብርሃም የወልድ እግዚአብሔር መሥዋዕትነት በሚፈጸምበት በኀልጎታ ሊሰዋው ይዞት ሄዷልና፡፡ ለወልደ እግዚአብሔር መንገድ ጠራጊ ሆኖአልና፡፡ የአንድ ልጁን መሠዋዕትነት ደስ ብሎት ባይቀበል ኖሮ ምሳሌውን ለማየት ባልበቃም ነበር፡፡ ምሥጢር ያዘለ የምሳሌ ደምን ለማፍሰስ ያንድ ልጁን መሥዋዕትነት ታግሶ ሦስት ቀን ተጓዘ እንጂ፡፡ ይስሐቅም መሠዋቱን አውቆ ባይታገሥ ኖሮ የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ለመሆን ባልበቃም ነበር፡፡ የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌነት ትዕግሥት ሰጠውና ታገሰ እንጂ ፡፡ ወልደ እግዚአብሔር የእኔ ፈቃድና የአንተ ፈቃድ አንድ ስለሆነ ያንተ ፈቃድ ይሁን እላለሁ፤ የእኔ ፈቃድ ይሁን አልልም፤ እንዳለ ይስሐቅም ለአባቱ ባንተ ፈቃድ ውስጥ ስላለሁ የወደድከውን ማድረግ ትችላለህ አለና በፈቃዱ እጁን ታሰረ፡፡ አብርሃምም ሳያዝንና ሳይራራ መጥባሕቱን ይዞ በመሠዊያው ላይ አስተኝቶ ልጄ ሆይ አንተ ቀድመህ ሂድና ከዚያ ቆየኝ ፤ እኔ መጥቼ እስክንገናኝ ድረስ የምትሄድበት አገር ምን ያህል ብዕል እንዳለ አታውቅምና ደስ ይበልህ ፤ እኔ ወደ ሰማይና ወደ



www.ethiopianortodox.org

ምድር ንጉሥ ነውና የምልክህ፡፡ ይስሐቅም አባት ሆይ እኔን ወደ በለጠ ክብር ስትልከኝ እኔ እንዴት ላዝን ይገባኛል፤ አሁን እኔን ያቀረብህለት ሞት አይደለም፡፡ ብዙ ትርፍ ሚገኝበት ሀብት የሚያስደስት ነው እንጂ ሞት ለሚቀበለው ሰው መራራ ነው ሲሉ ሰምቼ ነበር፡፡ እኔ ልቀበለው የቀረበልኝ ሞት ግን መዓዛው የሚያስደስት ጣዕሙ የሚጣፍጥ ነው ከዚህ ከምትቀበለው ሐዲስ ሕይወት የሚገኝበት ከሆነ የሞት ኀዘን አይስማማኝም ፡፡ ከመሥዋቴ የተነሣ ታላቅ ትምህርት ተገለጸልኝ፡፡ እንዲህ የቀረበልኝን ከመቀበል ወደ ኋላ አልልምና ለመስዋት የተዘጋጀህ ካህን እንደመሆን የታዘዘኽውን በእኔ ላይ ና ፈጽም አለው፡፡ አብርሃም መጥባሕቱን አንስቶ ሊሠዋው ቀረበ፡፡ ከማረዱ በፊት ባሳቡ አርዶ ደሙን አፍሷል፤ ቀጥሎም መጥባሕቱን ከይስሐቅ አንገት ላይ አድርጎ እስዋለሁ ሲል ተው የሚል ቃል ሰማ፡፡ አብርሃም አብርሃም ብሎ ጠርቶ መጥባሕቱን በይስሐቅ አንገት ላይ እንዳይስብ ከለከለው፡፡ መልአክም ታላቅ ምስጢር ፈጽመሃልና ልጄን እሰዋለሁ አትበል ፤ ባንተ ልጄ በይስሐቅ መሥዋዕት ዓለም አይድንምና፡፡ ሰይፋን ከይስሐቅ አንገት አንሣ፤ ፍታውና ይሂድ ፤ ከዚህ የምትታይ ምሥጢር አለችና ቀርበህ ተመልከት እውነተኛውን ምሳሌ እይ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል አንተ ዛሬ ለልጅህ እንዳላዘንክና እንዳልራራህ  እኔም ለአንድ ልጄ አላዝንለትም፡፡ ለዓለም ቤዛ አሳልፌ እሰጠዋለሁ አሁን ምሳሌውን ገልጬልህለውና አይተህ ደስ ይልህ ዘንድ ይህን እስከመጨረሻው ጠብቀው፤ ልጅህ ይስሐቅ ቢሠዋ ሲኦልን ሊማርክ የሲኦልን በር ሊከፍት ሊዘጋ አይችልም፡፡ አንድ የሚሆን የእኔ ልጅ ግን ሲኦል ያሉ ነፍሳትን ሁሉ ያወጣል ይስሐቅ ሞትን ድል መንሳት አይችልም፡፡ ጽኑ ሥልጣን ያለው ወልድ (ክርስቶስ) ግን ወደ ሲኦል ወርዶ አጋንንትን ድል ነሥቶ ነፍሳትን ያወጣል፡፡ ይስሐቅ መስዋዕት ሆኖ ሙታን ወዳሉበት ቢሄድ ምንም አይጠቅማቸውም፡፡ የኔ ልጅ ግን ወደ ሲኦል ወርዶ ያወጣቸዋል፡፡ የልጅህ መሥዋዕት ግን ወደ ሲኦል ወርዶ ያወጣቸዋል፡፡ የልጅህ መሥዋዕት ግን ለራሱም ለማንም አይጠቅመውምና ተወው፡፡ ወልደ እግዚአብሔር ነውና የፈጠረውን ፍጥረት የሚያድን አለው፡፡ አብርሃም የወልደ እግዚአብሔርን መሥዋዕትነት ምሳሌ ስለአየ ብዙ ደስ አለው፡፡ የስቅለትን ነገር እንደምን አድርጎ ይሆን? መቼ ይሆን? እያለ ሲያወጣ



www.ethiopianortodox.org

ሲወርድ በግ በእንጨት ላይ ታስሮ እና በበጉም አምሳል የጌታን ስቅለትን ሞቱን ትንሣኤውንም ገለጠለት፡፡ የክርስቶስን ነገር ልትረዳ ከፈለግህ መረዳት የምትችልበት ጊዜ አሁን ነውና አይተህ ደስ ይበልህ የሚፈጸምበትን ቀን ልታይ ከፈለግህ ሁሉም ከፊትህ አለልህ አለው፡፡

ከዚህ በኋላ አብርሃም ይስሐቅን ፈታው እና በጉን አሰረ፡፡ ሁለተኛ ምሳሌ ሆነለት፡፡ ይስሐቅም ከማሰሪያው እንደተፈታ ጌታ አምልኮ ጣዖትን ከሰው የመለየቱንና የማጥፋቱ ምሳሌ ነው፡፡ ጌታ መጥቶ ያለዘር ተወልዶ የኃጢአትን ማሰሪያ እስኪፈታው ድርስ ሰው ሁሉ በኃጢአት ታስሮ ነበርና ከዚህ በኋላ ለአብርሃም የምሳሌ ምሥጢር ሚፈጸምበትን በግ ሠዋ፡፡ በበጉም መሠዋት አንድ ልጁን ስለዳነለት ደስ አለው፡፡ ዳግመኛም አምላካችን ጌታችን የመዳናችን ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ ብሩክ ነው፡፡ ደስታን የሚሰጥ ኀዘንን የሚያርቅ ለእርሱ ክብር ምስጋና ይሁን ለዘለዓለሙ አሜን ፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር፡፡

አሜን፡፡



www.ethiopianortodox.org

www.ethiopianortodox.org